የአዲስ ኪዳን መቅድም



መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ

በሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ
መንፈሳዊ ኮሌጅ
የሃይማኖት መምህር

1977 ዓ.ም

www.ethiopianorthodox.org

መግቢያ

ቁጥር -፫

፫ኛ ፈተና ፥ የሐዋርያት ሥራ፤

1ኛ. ጸሐፊው፤ ይህን 2ኛውን ክፍል የታሪክ መጽሐፍ ወይም የሐ.ሥራን የጻፈ 3ኛውን ወንጌል የጻፈው ቅዱስ ሉቃስ እንደሆነ የታመነ ነው፤ ይኸንኑ ለሙሪዳት በወንጌሉ ላይ እንባሙለከተው ሁሉ በአቁር እንደመሩድም አደርጉ ስለዚህም መጽሐፍ ሲናገር እናገኘዋለን። 2ቱንም መጽሐፍት ላአንድ ቴዎፍሎስ ለተባለ ለአንድ ታላቅ ሰው መታሰቢያነትን ይሰጣሉና። በዚህ በሐ.ሥራ አጨራረስ አሰተያየት ወንጌላዊ እንደጻፈ ገልጠው መስክር ይጽፋሉ። 2ቱም መጻሕፍት ጋን ያሉን ግንኙነት እንየሳቸው በዚህ ሪንረዳ እንችላለን በኋላ ዘመን ተነሥተው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ከፍተኛ ጥናት/ፍርድ / ያደረጉት አበቶች ሁሉ እነዚህ 2ት መጻሕፍት በ1 ሰው እንደተጻፈ ይገለጠሉ። እንዲሁም የመጻሕፍት መቅደማቸው ከሚገለጠው ሌላ በውስጥ ያለው የመጨረሻ ዘመያቸው፤ የወረዱበት ነገር አሰካካቸው የአገላለጥ ሁኔታቸው በየጥታ እንደ

ገው ሐተታ ከተረዳን ስለዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ ማንነት ፍዙ ሐተታ አናደርገም፤ ጸሐፊው እርሱ እንደሆነ ተረድተናል።

2ኛ. የመጽሐፉ ዓላማ፤ 1 ሶሎ እንደሚያመለክተው የቅ.ሐዋርያትን ድካም ሥራ ከክርሶቶስ አርገት በኋላ ያደረጉትን የፈጸሙትን ሁሉ የሚገልጥ ነው። ምንም ሶሎ በኋላ በ2ኛው ጥሪት ጉዞት መጀመሪያ የተለጠፉ ቢሆንም ስሙና አፈጻጸሙ የተለየ ነው፤ ገለት ከመጀመሪያው ንድፍ ራቻ የሰውን ሕዋርያትን ተግባር የገለጠ ፀሐሰ እንጅ የተየረው ክፍለ ገን የሐዋርያውን የሚጓሉ ሰንና የርሱን ረዳቶች ሥራ ቢቻ ነው የሚናገር።

2. የመጽሐፉ ዓላማ በወንጌሉ ላይ "ከሙ ትኬሥት ራዕሃን ለአንዛዘ ማ ከረ ሰጠሽከ አምፈሉ." ሲነ ለአንዛዘ ራዕሃኖቹ ክርስቶስ እን ይሆነ ገጠሙ ሰዎ ነበርና አሁን በአንዛዘ ዘንድ የሚደረገውን ተአምራት የሚታየውን ራዕሃን ለመገለጥ ነው" ይነው በመሆኑ ይኸ መጽሐፍ የወንጌሪያው መጽሐፍ መጨያ የሚሰጥ ነው።

3. የመጽሐፉ ዓላማ መሰሉ የሚታየው ገን ራሱ ሉቃስ እንደገለጠው "ነገር ገን መንፈስ ቅዱስ በሰናንተ ላይ በመረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ" በዚያን ጊዜ በኢየሩሳሌም በአይሁዳ አገር ሁሉ በሰማርያ አስከ ምድር ፃርቻ ድረስ ምስክሮች ትሆኛላችሁ"/የሐ.ሥራ 1:8/:: የሚለው

www.ethiopianorthodox.org

ነው ያሉንያቱም ቀ.ጌናርያት በፈቱ ሰዱ በታ ተጠትነው መሄዳቸውን አ.ፃ
ንው በኢየሩሳሌም መኖረታቸውንና ቤተ ክርስቲያን ከሃገር ተነሥታ እገሌት
አንደተቋመች ያሰቤት የጢስጢን ይገው መጽሐፍ ቢቻ ነው። ከጵንጠዮስ
አገሰተ በፀሁዳ በስግርያ ጎደ ናድር መሮረሻ ድረስ ክርስትናው አንደተዳ
ረሰ የሃጹብ ጵጋሳስ ታሥሮ ሮኖ መገጢት ድረስ ይነገረናል።

ይሰንፍ በሱዴ አገሳለተ ይገሰጠዴ ከሁሉ በፊት ከጵንጠዮስጠ
አገዴት ያለ ነበሰቢሳዊ ሰጫት ስለ ክርስትና በኢየሩሳሌም ውሰተ አንደነ
በር፣ ከዚያኖ ነበሰቢሳዊ ሰጫት ሰዩበርድ ዛሉ ወደ ሰግርያ አንደ ደረሰ
ከሰግርያኖ ወደ አንጾኪያ፣ ከአንጾኪያኖ ወደ አፌሶን፣ ከዚያኖ ወደ ጥሮ
አዳ፣ ከዚያኖ ጎደ አቴና ጎደቆሮንቶስ፣ ከዚያኖ ወደሮም ቤተ መንግሥት
ገቢተ ነበሰቢሳዊ ትኮሀርት የሮኖን ቤተ መንግሥት አሰስ አተለየለየው
ድረስ ሉያስ በማይጠፉ አገሳለተ ሾፍ አስፋናጠሳናል። ክርስቶስ በ120
[illegible] ሮኖ ቤተ መንግሥት ድረስ ቢዙ ቱጋር ያለው ተከታይ ክስኮማፍሬት ድረስ
የሃጹስ ሉቃስ ዓሰገኖ ይጠነኑ ለማሰከት ሲሩ ይቸነ መጽሐፍ አንደጸፈ
ዔታሮናል። አንግዲህ የመጽፈፉ የና ዓሳማ የክርስትናን አነሣሥ ቀስ
በቀስ አንደሆነ በመግለጥና በተቂት ጊዜ የትኖ ዓለምን ሁሉ አንዳናረሰ
ለመግለጥ ነው።

የመጽፈ ይነገተኛ ክፍታ ነን ፈዘያችን አሰበቢቸሃል፣ ይሽውና
ቅጹስ ጵውለሰ ሮኖ መገቢቱን ኪተናገረ በኋሳ ሰለ ቅጹስ ጵውለሰኖ የመዉ
ረሻ ሁናቱ ነገሩ አያጋሰኖ፣ በሰዚህና የተለያዩ አሰተያየቶች በሰፉ ሰዩ
ሊቃውንት ዘንድ ዔስነዘፈሱ፣ 1. ፣ናሰቢት ቅጹስ ሉቃስ ሉሳ 3ኛ አፍሰ
መጽሐፍ ለማዘጋጀት አሰበ አሰኩሮ፣ ያለውን ጸሑፈን ዛገቱ ሉሳ ሲያዘጋጅ
ሞት ተጭት ይሆናል የሚሰ ነው። 2. ተገቱነኖ ዓሳማው አሰኩሮኖ ድረስ
ያለውን ቢቻ ሰፍ ለመቱው ኑሮ ይሆናል። በሐዚህ ያው አንደተረጸመ አቀ
ሞት ይሆናል። 3. ሉቃስ መጽፈን የጻፈው ሮኖ ሰለ ነው፣ ፉናጸበትኖ
ቅጹስ ጵሉሙስ ወደ ፍርድ ቨገጉ ሲይያርስ በ2 ዓመት ውስጥ ሉቃስ ሙቶ
ወይኖ አገር ለፃ ሂደ ይሆናል፣ ፖስገያቱኖ አንዲሁ በድገገት ያለማወቁለያ
መጽፈን ኪኑት አድርጉ አይተውኖ ነበርና።

www.ethiopianorthodox.org

መቶ የሚታየው ገነ ዓለማው ከኢየሩሳሌም እስከ ሮም የሆነውን ሁኔታ ብቻ ለመገለፅ ነበር፤ ይህውም ይታወቅ ዘንድ ቅዱስ ጳውሎስ ሮም ደርሰ ሥራ መጀመሩን በነፃ መስበኩን ይገልጣል፤ በዚሁም ይፈጸማልና፤ አ ርሱንም እንዲህ ሲል ይገልፃልና፦ "ጳውሎስ በተከራየው ቤት ሁለት ዓመት ሙሉ ተቀመጠ ወደርሱ የሚመጡትን ሁሉ ይቀበል ነበር፤ የእግዚአብሔር ነው መንግሥት በመስበክ ስለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንም ሳይከለክለው በ ድፍረት ያስተምር ነበር"/የሐ.ሥራ 28:30—31/::

የሐዋርያት ሥራ ዓላማን በሌላ መልኩ የሚመለከቱ ደግሞ አሉ፤ ይ ህውም የአይሁድ መንሀር በተቃለው በጴጥሮስና የአሐዛብ መንሀር በተቃለው በጳውሎስ መካከል ያለውን የሐሰብና የሥራ መለያየትና የጳጉሎስን ክርስ ቶስ አገለግሎት ለማሳየት የተጻፈ ነው የሚሉ አሉ፤ ናቸንያቱም ከመሠረቱ ይኖር በ2ቱ የትረፉት አበጋዘች በሆኑ ሐዋርያት መካከል መተናናት ነበርና::

ጋው አናገኘውለን /ገላት 2:11—14/:: እንዲሁም የበላይነትና የበታ ችነት ስሜት እንደነበረባቸው ከማንም የማንሱ አይደለሁም እያለ የቤተ ክርስቲያን አዕማድ የሚባሉት ጴጥሮስ፤ ያዕቆብ፤ ዮሐንስ ቢሆኑም ከእኔ አይበለጡም፤ እኔም ከነርሱ አላንስም ሲለ ገለጠ ሽፍ አናገኘውለን /ገላ 2:1—10/::

እንዲሁም በአይሁድ ቅንዓት የተነሣ ጳውሎስ ተከሰ ከስከሮም ሮድ ረሱን ገልጠ የተወው የአይሁድን ቢፋት ያየኘነት ለመገለጥ በአሕዛብ በኩል ገነ ያነ ያህል የወንገል ተሳቢነት እንዳለው ለመገለጥ እንደሆነ የሚ ገመቱ አሉ::

ሌሳው እውነተኛው አስተያየት ገነ ሉቃስ ይህን የጻፈው ክርስትና እንዲት እንደ ጀመረ የክርስትናው ተከታዮች በሆኑት ሁሉ እንዴት ያለ ችግር ይደርስባቸው እንደነበር ቅዱሳን ሐዋርያት ገነ እንዴት አድርገው መከራውን እንደተጋፈጡት ቅዱስ ጳውሎስም በኋላ የተጠራ ሲሆን ምን ያህል ለወንጌል ትምህርት እንደደከመ፤ እንደሠራ ለማሳየት ነው የሚሉ አሉ::

3. <u>የመጽሐፉ እውነተኛነት፤</u> የሐ.ሥራ በቅዱስ ሉቃስ እንደተጻፈ የጥንት ቤተ ክርስቲያን በአንድ ድምፅ መስክራለች የሙራቶሪያን ክዴክስም የሐ.ሥራ በሦስ በአንድ መጽሐፍ ተጠቃሉ እንደተዘጋጀ የዚህም ጸሐፊ ቅዱስ ሉቃስ እንደሆነ ይገለጣል:: እንዲሁም የጻፈበትን ምክንያት ሲገልጥ ለአንድ

www.ethiopianorthodox.org

ቴያፍሉስ ለተባለ ሰው የአምነት ቃላለጫ እንዲሆን ያደረገ መሆኑን በተጨማሪ መስኪሯለ። ይሁን እንጂ በጣም አሰፈላጊ የሆኑትን ሰለት ነገሮችን አስቀር ሸናፊ እነዚህም፡—

1. የጴጥሮስን ወደሮም መገባትና በዚያ መሞት፤
2. የጳውሎስን ከሮም መውጣትና ወደ ሌላ ሀገር መሔድ
3. የጳውሎስን ፅረፍት ዝርዝር ሁኔታ መገለጥ ናቸው።

የሀነው ሆኖ መጽሐፉ በሉቃስ መጻፉን ቅሬነጋስ /ለሙናፍቃን ተቃውሞ / ጠርጡሊያኖስ /ስለጽ/፤ የአስትንፎርያው ቀሌምንጦስ /አስተርጓቲስ / በዊለ ው መጽሐፉ አውሰቡ ዮስ ጣቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሉሶችም አባቶች እንዲሁ ሉቃስ እንደጸፈው መስክረው አስተላልፈውልናል።

ሉቃስ ያጻፈልን የሐዋርያት ሥራ የተቢለው መጽሐፍ ዋንታኛውን የ ክርስትና አመሠራረት የያዘ ነቃውን አሰረጀ ሆኖ የኖረበለን የታመነ ናን ኔ ነው።

አውሰቡ ዮስ በ3ኛው መቶ ዓመት ተነሥቶ ሙሉውን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ አሰከጻፈለን ድረስ ናነ፣ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ አፈነበረነ። ናነ ዘመኑ ትንሺ ቢሆን ከክርስቶስ ሐደት ጀምሮ ለሰከ 62 ዓ.ም. ያለውን ደህና አድርጉ ገልጨለን አናገኘዋለን።

<u>4. መቼ ርዔት ተጸፈ፤</u> የሐዋርያት ሥራ መቼ ወዴት አገደ ተጻፈ ለሚቀር ቡራን ትያቄ መልስ የሚሆነ የተረጋገጠ የታሪኩ ዘመን በታም የለውና፤ ግን የሚገመተው ቅዱስ ጳውሎስ ሮም በነበረበት ጊዜ በ2ቱ ዓመታት ውስጥ መሆ ን አለበት ይባላል ከ60—62 ዓ.ም. እንደሆነ ይገመታል። ከዚህ የበ ለጠ ዘገይቶ ተጽፎ እንደሆነ አይታወቅም። እንደ ዱቤፍ ጋሪደ ክርቱን አገላለፅ ከሆነ ግን በ93 ዓ.ም. አንደተጸፈ ይገመታል። አንዳንደችም ክርስትና የሮምን ቤተ መንግሥት ሠርጾ ገበተ ነበረበት ጊዜ ነው፤ ይህውም በንጉሠ ነገሥቱ በኔሮኒያኖስ የአጉት ሰጀ ፍሳቢዮስ ከለጫንት በተባለው ጊዜ ነው፤ እናሱም በውሸት ቱታፍሉስ አየተቢለ የተመራው ነው ሲለ ገለጠ ሳናል /.....፡፡

<u>5. የሐ.ሥራ የተለየ ጠቢቱ፤</u>

ይህ መጽሐፍ ዝርረ መንፈስ ቅዱስ /የመንፈስ ቅዱስ ሥራ / ዙሉ ለሰየም ይገባዋለ፤ ናሉንያቱም ከመጀመሪያው አንስቶ የመንፈስ ቅዱስን ገበና

www.ethiopianorthodox.org

በተለያየ መልክ የተረጎመውን ይናገራሉና:: ቅዱሳን ሐዋርያት የመንፈስ ቅዱስ መሣሪያያችኽ ሆነው የሠሩትንና የተሠራላቸውን የሚገለጥልን ይበው መጽሐፍ ቤቻ ነው፤ እሱም ከልንጠየስጠ ይጀምርና ይሄዳል /የሐ.ሥራ 2:1—27/ ቅዱሳን ሐዋርያት ቅዱስ መንፈስን እንደተሞሉ /የሐ.ሥራ 4:23—31/:: በመንፈስ ቅዱስ ላይ በደል የፈጸሙት እንደተቀጣ ይነገረናልና /5:1—11/ የሰማርያ ሰዎች ቅዱስ መንፈስን እንደተሞሉ /8:14—17/:: ፊልጶስ በመንፈስ ቅዱስ ተመሰቶ የፈጸመውን ይገልጥልናል /8:29/:: የቆርኔሊዎስ ንና የቤተሰቡን ቅዱስ መንፈስን መቀበል ይገልጥልናል /10:44—48/: የበርናባስንና የሳኅልን በመንፈስ ቅዱስ መጠራት ይገልጥልናል /13:1—4/

ቅዱስ ሲኖዶስ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ ጉባኔ መስጠቱን ይነገረናል /15:28/:: መንፈስ ቅዱስ ለጳውሎስ ለሥራው መቃናትን እንደሰጠው ይነገረናል /16:6—7/:: በኤፌሶን የነበረት ተማሪዎች ቅዱስ መንፈስን [illegible] /19:1—6/:: ጳውሎስ [illegible] ለጳውሎስ መንፈስ ቅዱስ መገለጡን ይነገረናል /20:22፤21:11/::

ካህናት በመንፈስ ቅዱስ ተመርጠው ወደ ዘህነታዊ አገለገሉት እንደተመደቡ ያስረዳናል /20:28/:: ይህንን የመሰለ የቅዱስ መንፈስን ሥራ ዘርዝሮ ያስረዳልና::

ሉላው የመጽሐፈ ጸበኃ ተንታኒውን የኪርስትናን መለኪና ጠቢይዕ ስለሚገልጥሉን የተለየ የኪርስትና መጽሐፍ ይባላል:: ይሰውና ከመጀመሪያው አንሥቶ እስከ አርገት ያለውን ሰፍኖ ካስተሳሰፈልን በኋላ ከጴራቅሊጦስ ጀምሮ መጀመሪያውን የክርስትና ስበከት የመጀመሪያውን የቤተ ክርስቲያን መሠረትና ዝረት የቤተ ክርስቲያን ታሪት የመጀመሪያውንም ተመቀት ይገለጥሳናል

የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ስያት የመጀመሪያያቹን ሰማዕታት የመጀመሪያውን ሐዋርያዊ ጉዞ ከአይሁድ ዓለም ወጥቶ የክርስትናን ጉዞ ወደ አሕዛብ መሄዱን የመጀመሪያያቹን ዲያቆናት ምርጫና ሹመት ሌላም ይህንን የመሰለ ዛሬ ላለኽው ቤተ ክርስቲያን ጥሰሉ የሚሆነውን ይገለጥልናል:: ይሽን የመሰለ ትምህርት ያለት ቤተ ክርስቲያን ከጦን ተነሥታ ከፉን እንደደረሰቸ የሚያስረዳን ስለሆነ የመጽሐፉ ጠቃሚነት በጣም ከፍ ያለ ነው::

www.ethiopianorthodox.org

ክፍል 3 የሐዲስ ኪዳን የትርጓሜ መጻሕፍት

ርዕስ 1 መሰከረ ታት

1. የመሰከረ ታት ቁጥር

መሰከረ ታት ዝርዝው የሚመረት የሐዲስ ኪዳን ክፍል የሚሆኑ መጻሕፍት ናቸው፤ ከነዚህ የትርጓሜ መጻሕፍት እየተጠሉ የሚመረት ናቸው። በአለፉት ክፍሎች የተናገርንላቸው 5 መጻሕፍት ነን የታሪክ መጻሕፍት አንደ ሚባሉ አትተንላቸዋል።

አነሱ የታሪክ መጻሕፍት ስለተጠሉ ታሪክን ብቻ የተከተሉ ታሪክ ንጉ ብቻ የተሸከሙ አይደሉም፤ ትርጓሜም በሰፊው ይገኝበቸዋል አንጂ። መሠረተ ሃይማኖት፤ ሥነ ምግባር ሌሎችም ይህን የመሰሉት ትርጓሜዎች ሁሉ የሚገኙባቸው ክፍሎች ናቸውና።

[illegible] ፍት ነን የሚይዝ ክፍል ስለሆነ የትርጓሜ ክፍል ዝሉ ይጨራል። በዚህ በመሰከረ ክፍል የተዘጋጁት መጻሕፍት የተጻፉት ለነሱ ስጋቸው፤ ለቤተ ሰቡ አ፤ ለቤተ ክርስቲያን /ለማነበር / ነው፤ ስለዚህ በቀጥታ ትርጓሜ ተግሣጽ፤ ምክር፤ መሠረተ ሃይማኖት ስለሚገኝባቸው የትርጓሜ ክፍል መሆ ናቸው ጉሉተ ይታያል።

ከ27 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ 21ዱ በመሰከረ ሥነ የተጻፉ መጻሕፍት ናቸው፤ ከነዚህ ውስጥ 13ቱ ሮም 14ቱ በጳውሎስ የተጻፉ ናቸው፤ ሌሎች ነን በ ተለያዩ ስጋቸው የተጻፉ ናቸው፤ ለመስል 2ቱ የጴጥሮስ፤ 3ቱ የዮሐንስ፤ 1ዱ የያዕቆብ፤ አንዱ የይሁዳ መሰከረ ተች ናቸው።

እነዚህ የመጠረቫያቱ 7ቱ መሰከረ ታት ጠቅላላ /ካቶሊክ / መሰከረ ታት ይባላሉ፤ ምክንያቱም ለተለየ ሥገን ሮም ለተለየ በጭ የተጻፈ ሳይሆን በአጠቃላይ ሰውዕመናን /ለአገቢ ያን / ሁሉ የተጻፉ ናቸውና።

በነዚህ በመሰከረ ት መሰረ በተጻፉ መጻሕፍት ቤዙ ነባጅ ይፈለጋቢ ቸው ነበር፤ ጣለት ትጹስ ሳጭሉስ እየተመላለሰ ያስተማረቢ ቸው አህጉር /አሳያተ ክርስቲያናት/ ያሸናናቢ ቸው፤ ተገሰጸና ምክር እዝናት ይሰጥቢ ቸው፤

www.ethiopianorthodox.org

ጥያቄ ደቀርቤባቸው ልደ ሐዲስ ኦሪቶዶክሳዊት ሃይማኖታቸው ነበር።

እነዚህም መልእክቶች እንደሚታወቁ የይሁዳስ መጻጻፊያ ሳይሆኑ እስከ ትንሣኤ እግዚአብሔር እንደመሆናቸው የእኀዚአብሔር ፈቃድ ተቃውሞአቸው እንዲሠሩ ቅዱስ ጴጥሮስ እግዚአብሔር ፈቃዱ የታመኑ ክህሎት ከትጉኅ መጻሕፍት ውስጥ ገዝቶ የተኖረ ቀኖናቸው ናቸው።

ከዚያቸን መሪአኪታት የጻፈ ጳውሎስ መሆኑን ገለጠናል፤ ስለዚህ የርሱን መልእክቶች ከመመርመራችን በፊት ጳውሎስ ማነው? ምንስ ነበር? እንዴት እነዚህን መልእክታት ሊጽፍ ፈለገ፤ ሌላም እነዚህን የመሰሉትን ጥያቄዎች መመለስና ሐተታውን ማራዘም አስፈላጊ ስለሆነ ወደ ጳውሎስ የሕይወት ታሪክ እንመለሳለን።

2. ቅዱስ ጳውሎስ ከተወለደበት ጊዜ እንስቶ ለወንጌል አስከተጠራበት ጊዜ፤

ጳውሎስ የቀደም ስሙ ሳውል ነበር፤ ትርጉሙም የእግዚአብሔር ጥያቄ ማለት ነው፤ ይኸው ሰው የተወለደበት አገር በኪልቅያ አውራጃ የምትገኘ ጠርሴስ የተባለች ከተማ ናት /ሐዋ. ሥራ 21:39፤22:3/።

ጳውሎስ ከሀብታሞች ወገን እንደመወለዱ በሃይማኖትም በሕሉ ደገም የፈሪሳዊያን ወገን ነበር፤ ጠንቅቆም ከቤንያሚን ወገን እንደሚወለድ ራሱ መስክሮ ጽፏል ፊልጵ 11:4 ራሱ የርግዪያን ዜግነት የነበረው ሰው ነው፤ ይኸውም ሲወለድ ጀምሮ የነበረው መሆኑን ሉቃስ ይገለጥልናል /የሐ.ሥራ 9: 11፤ 25:13፤9:16:35:22፤ ፳፪:፳፭:፭፤ ሮሜ ፲፮:፯፤ ፈሊጵ 3:5/።

ጳውሎስ ታላቅ አእምሮ የነበረው፤ የጣስተዋል ኃይል የተሰጠው ትልቅ ፍላጐትም የነበረው ሰው ነበር።

ጣላጀቹ በልጅነቱ ወደ ኢየሩሳሌም ወስደው ለታላቁ የሕግ መምህር ለገማልያል ሰጡት፤ በአይሁድም የአስተዳደግ ሥርዓት አሳደጉት /የሐ.ሥራ 5:34፤22:3/።

ዕብራዊያን ልጆቻቸውን በሚያስተምሩበት ጊዜ ሐዲስ ዲስ ጥበብ እድ አዘረው እንደሚያስተምሯቸው ሁሉ ጳውሎስም ከተለመ ትምህርት ሌላ የአጀ ሥራ እንደ ድንኳን መስፋት ያለ ተምሮ ነበር /የሐ.ሥራ 22:3/።

www.ethiopianorthodox.org

እሥራኤል በልዩ ልዩ ምክንያት ከኢየሩሳሌም ውጭ ተበትነው ይኖረ
ነበር፤ እንደዚሁም ሁሉ የቅዱስ ጳውሎስ ቤተሰቦች እሥራኤላዊያን ሲሆኑ
ከኢየሩሳሌም ውጭ የቂልቅያ አውራጃ ጠርሴስ በምትሆን በጠርሴስ ይኖረ ነበር፤
ይህች ጠርሴስ የተባለች ከተማ በዚያን ጊዜ ከፍ ያለችና ሰው ጥር ነበረች
ማለት የሐገና የፍልስፍና ትምህርት ቤቶች ይገኝባት ነበር። ቅዱስ ጳው
ሎስም ከነዚህ ትምህርቶች ብዙውን ሐገን በዚያ እንደፈጸመ ይገመታል።

ቅዱስ ጳውሎስ ለአባቶቹ ሐገ ቀናተኛ ሆኖ በሚሠራበት ጊዜ የክር
ስቲያን ትምህርትም በበኩሉ በሰፊው ይነገር ነበር። ስለዚህም ጳውሎስ
ለአባቶቹ ሐገ ቀናተኛ ሆኖ ክርስቲያኖችን ከሚያስተምረበት አገር አስወጥተ
ለማሰደድ ቍርጥ ሃሳቡ አድርጉ ተነሣ፤ ክርስቲያኖችም ከጳውሎስና ከሌሎችም
አይሁድ ፕሳቻ የተነሣ ከኢየሩሳሌም እየወጡ ወደ ልዩ ልዩ በታዎች ይሰደዱ
ነበር /ገላት 1፡13—14/።

3. ቅዱስ ጳውሎስ በተአምራት እንደተመለሰ፤ [illegible]
ፋኖስ ም ት የተነሣ ወደ ልዩ ልዩ በታ ተበትነው ነበር፤ በተለይም ወደ
ሶርያ ከተማ ወደ ደማስቆ በዙያች ክርስቲያኖች ገቡና ብዙ አይሁዶችን አ
ጠመቁ፤ ሳውል ይህን በሰማ ጊዜ ወደ ሊቀ ካህናቱ ሂደ በኢየሩሳሌም እንደ
ሚያደርገው በአንጾኪያም ክርስቲያን የሆኑትን ሁሉ ማንዱንም ሴቱንም ትፈ-
ቅንም ትንሹንም አያመረ ወደ ኢየሩሳሌም ለማምጣት ፈቃድ ጠየቀ። በዚያን
ጊዜ የኢየሩሳሌም ሊቀ ካህናት በፍልስጥኤምም ሆነ ወይም በማንኛውም ሀገር
የሚገኙ አይሁድ ሁሉ ከሃይማኖታቸው ሲናወጡ ይዳኘ ዘንድ ከርማ መንግሥት
ፈቃድ ስለነበረው ሳውል ለሃይማኖቱ በሳየው ቅናት ደስ ተሰኝቶ የጠየቀውን
ፈቃድ ሰጥቶ መርቆ ሰደደው።

ሳውልም አሠረው ከሚጓዙት ጋር ከደማስቆ በር ሲደርስ ድንገት
ከሰማይ መብረቅ ወረደና መታው፤ ወደቀም ዓይኖቹም ታወሩ፤ /የሐ.ሥራ 9፡
4—28፤ 22፡3—12/። ከሰማይም ሳውል ሳውል ለምን ታሰድደኛለህ የሚል ድ
ምፅ ሰማ፤ ሳውልም አንተ ማነህ? አለው፤ ጌታም እኔ የናዝሬቱ ኢ
የሱስ አንተ የምታሰድደኝ ነኝ አለው። ወደ ከተማውም ሂድ የምትደነበትን
ታገኛለህ ብሉ ጌታ አሰናናው። ከወደቀበትም ተነሥቶ አብረውት በነበረ
ሰዎች እየተመራ ወደ ከተማው ገባ፤ አብረውት የነበረት ሰዎች ድምጹን ይ
ሰሙ ነበር እንጂ ያዩት ነገር ከተ አላነበረም።

www.ethiopianorthodox.org

ከከተማው ዝቶ 3 ቀን ሙሉ እህል ሳይበላ ውሀ ሳይጠጣ በነበተ። በዚያ ከተማ ሐናንያ የተባለ የጌታ ተከታይ ከሰባ ሁለት አርድእት ውስጥ የሚሆን ይኖር ነበር። ጌታ በሌሊት ሳውሰን እንዲያጠምቀው ነገረው፤ ሐናንያም ጌታ እንዳመለከተው ሳውሰ ካለበት ቤት ድረስ ሂደ አጠመቀው እርሱም በተጠመቀ ጊዜ አይኑ በራለት፤ ሥጢር ተገለጸለት፤ መንፈስና ኑዱስ አደረበትና ሳዲሱ ሃይማኖት ቀናተኛ ሆኖ ሰዮሰ ሰደር ሳይሰ ዕለቱን ማስ ተማር ጀመረ።

ኩርስቶስ ተጠምቆ ሰዮሬ ሰያር ሳይሬ ዕለቱን ገዳም እንደገባ ሳውሬም ከተጠመቀ በኋላ ዋቂት ቀን በደማስቆ ቆይቶ ወደ አረቢያ ሶድረ በዓ ሂደ ሰስት ዓመት ተቀምጠ ሱባዔውን ፈጸመ /ገላት 1:17/። እንደገና ወደ ደማስቆ ተመሰስ ሲያስተምር ብዙ አይሁድና አሕዛብ አሙኑ ተጠቀ፤ ነገር ግን አይሁድ በርሱ መመለስ ሲያዙኑ እርሱ ማስመኑን በሰመ ጊዜ በ[illegible] በመዓዝ ትም የደማስቆን በር ይጠብቁ ነበር፤ ክርስቲያኖች ግን ይስን በሰመ ጊዜ በቤቱ መስኮት አውጥተው በቅርጫት አድርገው አሸልከው ሰደዱት። እርሱም ወደ ኢየሩሳሌም ወረደ ከዚያም ወርደ ሐዋርያትን /ለማገኘት/ ይፈልግ ጀመረ። ሐዋርያት ግን ቀደሞ የክርስቲያን ጠላት መሆኑን በማወቃቸው ይሸሹት ነበር፤ ሐናንያንና በርናባስን አግኝተው በክርስቶስ ማመኑን እስኪረዱለት ድረስ። በኢየሩሳሌም ዋቂት ወራት ከተቀመጠ በኋላ ወደሀገሩ ወደጠርሴስ ሄደ፤ ከዚያም ገንዘቡን አሰናድቶ ለድኃ የሚሰጠውን ሰዋቶ ዘመዶቹን ተሰናብቶ ወደ አንጾኪያ ሄደ።

4. <u>የጴጥሮስ ጴውሎስ የስብከት ዘዴ፤</u> አንድ ገበሬ መሬቱ ለዘራ፤ ዘሩም ለመሬቱ ተስማሚ መሆኑን አውቆ አነዚዘራ ጴውሎስም ትምህርቱ ለሕዝቡ፤ ሕዝቡ ለትምህርቱ ተስማሚ የሚሆነበትን በታና ጊዜ እየመረጠ የትምህርቱንና ዓይነት እያሻሻለ ይሰጣቸው ነበር። የሚሰበክባቸው በታያች በዚያን ጊዜ በዓለም የታወቁና ብዙ ሕዝብ የሚገኝባቸው አህጉር /ከተማያች/ ነበረ፤ ለምሳሌ አንጾኪያ፤ አፌሰን፤ ተሰሎንቄ፤ ቆሮንቶስ፤ አቴና፤ ሮም ኦ የመሳሰሉት ነበረ፤። ደገሞ የሚያስተምረው በተለያየ ሰው በተሰ[illegible] በታ በሙሐዲ፤ በአደባባይ፤ በገቢያ፤ በቲያትር በታ ነበር። በየደረሰ በትም አገር በመጀመሪያ የሚገባውና የሚያስተምረው በአይሁድ መካከል ነበ[illegible]

www.ethiopianorthodox.org

ሲለዚህም ከነርሱ ውስጥ ኤርስቲያን ያየረጋቸው በዙያች ነበረ፣ ይሁን እንጂ ከአሕዛብም ውስጥ ያሳመናቸው እጅግ በጣም ብዙ ነበረ፣ በዚህም ምክንያት የአሕዛብ መምህር ይባላል። ጳውሎስ በአመነ ጊዜ ኤርስቲያኖች የሚገኙ በኢየሩሳሌምና በአካባቢዋ ብቻ ነበር፣ ከኢየሩሳሌም ውጭ እንደ ሰርያ፣ ቢሉት አገሮች ብቻ ነበር፣ ነገ ጳውሎስ በትጋት ከማስተማረ የተነሣ በኤርሱ ጊዜ ከኢየሩሳሌም አንስቶ እስከ አስጳንያ ያሉት አገሮች ኤርስትናን ተቀብለው በተ ኤርስቲያን አቋቁመው ተገኝተዋል። እየደረሰ በቃል ካስተማራቸው ይሉት በኋላ በመልእኬት መልክ የአስተላለፋቸውና ያናመናቸው እጅግ ብዙያች ናቸው፣ ይበንንም ሁሉ ሰሠራ ይበንንም ሁሉ ሀገር ሲዘር ከቶ እንድ ቀን ሰውን አበቸገር ከሰውም ገንዘብ ወስደ አያውቅም። በአፍ እየሠራ ራሱንም ሰውንም ይረዳ ነበር እንጂ /1ኛ. ቆሮ 4:12፣9፣ 2ኛ ቆሮ 11:7፣ የሐ.ሥራ 20:34፣ 1ተሰሉ. 2:9/። እንዲህ አድርጉ ተለአከውን ሲፈጽም ገን ይበን ቃል ተናገረ" መለካሙን ገዴ ተጋደሉ፣ ፈዟኖንም ዘረፉ፣ ሃይማኖቴንም ጠበቅሁ፣ እንግዲህስ ያ ጸድቅ ፈሬጅ ናጋየን ይከፍለኛል ለአኔም ብቻ አይደለ መገለጡን ለሚወዱ ሁሉ ክንጂ" /2ኛ ጢሞ.4:7—8/።

<u>5. የጳዱስ ጳውሎስ ሐዋርያዊ ጉዞ፣</u> ጳዱስ ጳውሎስ ወደ ኤርስትና ሃይማኖት ከገባ በኋላ ወንጌሉን ለማስተማር ብዙ አገሮችን ዙሯል፣ እነዚህንም አገሮች ለመቀጠር ብዙ ደክሟን የሚያመጣቡን በመሆኑ በአፄረ ለመረዳት 3 ሐዋርያዊ ጉዞን አንዳደረገ እንገልጠለን፣ ነገር ግን 4ኛም ጉዞ አደርጉ የሚሉ አሉ። ይሁን እንጂ የዓለም አፈ ያተ ኤርስቲያናት በቡዚት የመጠመት በ3ቱ ሐዋርያዊ ጉዞ ብቻ ነው። አነርሱም የሚከተሉት ናቸው።

<u>1ኛ ሐዋርያዊ ጉዞ፣</u> በ45 ዓመት ከኤርስቶስ ሬደት በኋላ በርናባስን ጢሮስን አስከትሉ ከአንጾኪያ ወደ ቆጵርስ ወረደ፣ በዚያም ሰላሚና በሚባሉ የቆጵርስ ከተማዎች ትምህርት ሲያስተምር ታአምራት ሲያደርግ ቆየለ፣ ጳውሎስ የሚለውን የመጠሪያ ስሩም በዚሁ አገኘ፣ ስለዚህ ኤዲህ ጳውሎስ እንጂ ሰውለ ሲለው አናገኘውም ከዚህም በኋላ ወደተሩሄደ፣ ከዚያ ሲደርስ ገነ ጳርቆስ መከራውን ተሰቅቆ ተመለሰ። በርናባስን አስከትሉ ዛሬ ቱርክ የተባለውን አገር ፍርጊያ፣ ጲ ዲያ አውራጃ የምትሆነ አንጾኪያን ኢቆንዮንን ሰስተራን ደርቤን

www.ethiopianorthodox.org

ከጌደ ብኋላ ክንደገና ቦንዚሁ አገሮች ሒድና አያስተማረ ወደ አንጾኪያ ተመለሰ:: /የሐ.ሥራ 14ናውን ምዕራፍ ተመልከት/ አንጾኪያ እንደደረሰ ከአይሁድና ከአረማዊያን ወገን ክርስቲያን የሆኑት ወገኖች ተጣልቱው አገኘ ፡ክንያቱም አይሁድ አረማዊያንን በክርስቶስ ቤታምኑና ቤትጠቁም ካሉተገ ዘራችሁ ምን ይረባችኋል? አጋሉ ያደክሟቸው ነበርና:: ጳውሎስ ይህን ሁ ከት ለማረጋጋት ሲል ሐዋርያት ጉባኤከት ወደ ኢየሩሳሌም ወረደና ሁኔ ታውን አስረዳ፣ ሐዋርያትም ተሰብሰበው የመጀመሪያውን ሲኖዶስ ከክርስቶስ ዕደት በኋላ በ5ኛው ዓመት አድርገው ነበር:: በዚህም ጊዜ ቤዙ ከተወያዩ በኋላ የመጠረሻ ውሳኔ አድርገው የተስማሙበት የሚከተለው ነበር፣ ከእሙት ከርኩበት ጣኦት ከማፉለቤ ይህንም የመሰለ ጸያፍ ነገር ከመሥራት ቤቻ መራቅ እንጅ ሌላ ሰው ሠራሽ ሕግ የሚያስፈልግ፣ መሆኑ ተወሰነ:: ገዝረ ትም በቤሉይ ዲግ ውስጥ ኃይል ቢኖረውም በሐዲስ ሕግ በታ እንደለለው ወ ሰኑ፣ ጳውሎስም ይህን ውሣኔ ወደ አንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ከዐረሰ በኋላ ሁለተኛውን ሐዋርያዊ ጉዞ ጀመረ::

<u>2ኛ ሐዋርያዊ ጉዞ፣</u> በሁለተኛው ሐዋርያዊ ጉዞው ሲላስን ጢሞቴዎስን ሉቃስን ይዞ ከክርስቶስ ዕደት በኋላ በ53 ዓ.ም. ፍርገያ፣ ቤታንያ፣ ሚስያ የ ሚባሉትን አገሮች አየጠና ተሻገረና ብዙ ቤተ ክርስቲያናትን አቋቋመ እነዚህም ፊሊጲስዩስ፣ ተሰሎንቄ፣ ቤርያ፣ አቴና፣ ቆሮንቶስ ናቸው:: ከዚያ በኋላ በታናሺ እስያ አድርጉ አፌሰንን እየሰበከ ወደ አንጾኪያ ተመለሰ::

<u>3ኛ ሐዋርያዊ ጉዞ፣</u> ይህ 3ኛው ሐዋርያዊ ጉዞ እንደሐዋርያት ሥራ አገ ላለጥ የመጠረሻው ያደርገዋል፣ አርሱንም አንደጢሞቴዎስና፣ ጳውሎስ በ3ኛ ሐዋርያዊ ጉዞው ሉቃስን፣ ጢሞቴዎስን፣ ቲቶን አስከትሉ በኋላ ጊዜ መነሻው ከሆነች ከአንጾኪያ ይነሣል፣ ይሽውም በ56 ዓ.ም. ገደማ ይሆናል:: ከዚያም ተነሥቶ ገላትያን፣ ፍርገያን፣ አያስተማረ ወደ አፌሰን ወረደ:: በአፌሰንም 2 ዓመት ተኩል ተቀምጠ ከኖየ በኋላ በጥሮ አዳ አድርጉ ወደመቄዶንያ ሄደ:: በዚያም በ2ኛው ሐዋርያዊው ጉዞው ጊዜ ያቋቋማቸውን አዲያተ ክርስቲያናት አደገጠ አያስተማረም ኖየ:: አሰልቦሪኖን የተቢለውንም አገር ሰመጎኘት የቻለው በዚህን ጊዜ ነው፣ /ሮሜ 16:9/

www.ethiopianorthodox.org

ጣለት ከዚያ ሲነሣ በአፈሬሪቶን አደሶጉ ወደ ቶሮንቶስ ጋርጿልና፤ በቶሮ ንቶስም 3 ወራት ቪያስቶሮር ከቶየ በኋላ ወደሰርያ ለመመለስ ተገደደ፤ ምክንያቱም አይሁድ አሲኒተው ይጠሉት ነበርና::

አንደገናም ከቶሮንቶስ ወደመቄዶንያ ሔደ፤ በጥሮአዳ አድርጉ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ /የሐ.ሥራ 20:13/:: በዚህ በመዉረሻው ጨርያዊ ጉዞ ጊዜ ለ4 ዓመታት ያህል ሲዘዋወር ቆይቷል፤ ይህም እስከ 59 አና 60 ዓ.ም. መሆኑ ነው::

ኢየሩሳሌምም ያርሰ በነበረው ቪስዓት መሠረት ወደቤተ መቅደስ ዝተ አይሁድ በቅንዓት ተነሣሠቡት፤ እሻቸውንም በሳዱ አነሠበት በቁጥራቸው ሥር አየሉት /የሐ.ሥራ /:: ከዚህም የቢስ አስሰፈው በሮማዊያን እንጅ አስገቡት፤ ከዚህ በኋላ ገነ የመዉረሻ የዕረፍት በታው ወደ ሆነችው ወደሮም ታሥር ሔደ፤ ይህም ሮም ሲገባ 62 ዓ.ም. ነበር::

6. የጳዉስ [illegible] እንደገና በሮሙ ገንዘር ቤት ..... ሊጠይቀው የሚጣውን ሁሉ እየተቀበለ እያነጋገረ 2 ዓመት ያህል ኖየ:: /የሐ.ሥራ 28:31/ ከዚያም በኋላ የነርስቲያን መገረፊያ የተባለው ወ ካኙ ነሮን አስይዘ አንገቱን አስመታውና /አስቆረጠውና/ በሰማእትነት ሞተ::

" የማታ ማታ አውነት ይረታ" እንደሚባለው ሁሉ በዚያን ጊዜ ካህ ናቱም፤ ነገሥታቱም፤ ተራው ሕዝቡም በጠላትነት ተነሥቶ ዕለት እንደሚታረድ በገ ይሙት ይሙት ቢሉም ሥራው ደገና አውነተኛ የሆነ ጳውሎስ እነሆ ሁሉ ንም ረትቶ በነገሥታቱ ዘንድ ሲከበር፤ በካህናቱም ዘንድ ሲመሰገን፤ በሕ ዝቡ ዘንድ ሲታፈር ይገኛል:: ሥራው አውነተኛ የሆነ ሰው ሁሉ እንደዚህ ይከበራል፤ ይታረሌል:: " ሐሰትና ስንቅ ለጊዜው ይዉ,ዳል ቆይቶ ግን ይናሳል" እንደሚባለው ሐሰት የሚያደርጉ ሰዎች ለጊዜው ከፍ,ረው፤ ገነው ይታያሉ፤ በኋላ ገነ ቦሮ አጠፊሬቸው የከፉ፤ ታሪካቸው የጠፋ፤ ይሆናል:: ጳውሎስ በዚህ በአጭር ጊዜ ውይያቱ ለፍ,ዙ ዋቅም የሚውሉ 14 መልእክቶችን ጽፍለን ሔዷል፤ እነርሱም የሚከተሉት ና ቸው::

7. የጳውሎስ መልእክታት፤ በመልእክታት መለክ ከተጻፉት የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ አበዛኖቻቹ የጳዉስ ጳውሎስ የእጅ ጽሑፎች ና ቸው::

www.ethiopianorthodox.org

የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት በጥንት ዘመን ፪ት ክፍለ ይከፈሉ ነበር፣ እነዚህም የመጀመሪያዎቹ ክፍሎቹ ወንጌል ሐዲሳዊ አተ ልኩት አጎኘቱ ነበር፤ ለዚህ ምክንያት ነው የሮሜ መልእክት የመጀመ ሪያውን ፬ት ብቻ ብታገኝ የቻለችው ይኸች መልክክት በተለይ እግዚአብሔር ስለ ምት ቀጠር ከወንጌል ጋርም ለማገናኘት ይጣለት ቅድሚያን ይዛ ትቆሟቸዋ ::

ሌሎች የመጨረሻዎች ግን እንዲሁ መጻሕፍት ተበለው ይጠሩ ነበር :: እያንዳንዱ መልእክት ግን ዘመኑን ተከትሉ ቀደም ተከ ታሉን ጠብቀ የተጠ ረዘ አይደለም፤ ወደ ፊት እያንዳንዱን መልእክት ይምናጠኖበት፣ ጊዜ መኝ ወጌት እንደተጻፈ ስለምንመረምር ቀደም ተከ ተሉ አለመጠበቁን ይዚያው እና ቀርለን ::

አሁን ግን ተጠርዘ የምናገኘው ተዘዋውሮ እንደመልእክቱ ክፍል ነት፤ እንደተሰበሰበት ቤተ ክርስቲያንም ታላቅ ነት ሆኖ እናገኘዋለን :: የመልእክታቱን የአጻጻፋቸውን ቅደም ተከ ተል ለማግኘት ስንፈልግ መልእክ ታቱን ፫4 ዓይነት እንከፍላቸዋለን :: የመጀመሪያው ክፍል 2 ቱን ወደ ተሰሎንቄ የተጻፉትን መልእክታት ይይዛል፤ እነዚህም ፳2ኛው የሐዋርያዊ ዝዘው ጊዜ ፹52 እና ፹53 ዓ.ም እንደተጻፉ የሚገመቱ ናቸው :: እነ ዚህም መልእክታት ምስጢረ ምጽአትን የሚመለከቱ ስለ ምሥጢረ ምጽአት የሚናገሩ ናቸው ::

ሁለተኛው ክፍል 2 ቱን የቆሮንቶስ መልእክታትንና ያገላትያን፤ የሮሜን መልእክታት ይይዛል :: እነዚህም ቢ3ኛው የሐዋርያዊ ዝዘው ጊዜ ቀይ ተው ፹56 እና ፹58 ዓ.ም መካከል እንደተጻፉ የሚገመቱ ናቸው :: በነዚህም ዘመናት ከመቸውም ይልቅ አይሁድ ቤተ ክርስቲያንን ያተቃወሙ በት የጳውሎስንም ዝና ያበላሹበት ጊዜ ነበር፤ እርሱ ደግሞ እነርሱን ይዘልፍበት ሕጋቸውን ይቃወምበት የነበረ ጊዜ ነበር :: ስለዚህ እነዚህ መልእክታት የታለ ጠርነትን የሚያነሣሱ ተቃውሞን የሚያመጡ እንደሆኑ ያመለክታሉ ::

www.ethiopianorthodox.org

የቃለ ጠር ነት በበዛተ ከጫታይቢቸው መልእክታት ውስጥ ወደ ገላ
ትያ የተላከቸው መልእክት ናት፤ በዚህም የክርስቶስን ትምህርተ አስፋፋተ
የአይሁድን ጥፋት ገለጠ የጻረበተ ነው።።

ቡዚሰ ቲኖው ኩፋለ ጳውሎስ በመጀመሪያው በሮም አሥራተ ጊዜ በ62
አና በ63 ዓ.ም የተጻፉ ናቸው። አ ነዚህም ቦደፊልጵስዩስ ወደ ኤፌሶን፤
ወደ ቆላስያስ፤ ወደ ፊሊሞና የተጻፉ ናቸው። አ ነዚህ መጨረሻያቸ ስለ
ክርስቶስ ማን ነት አስፋፍተው ይዘው የጫገኙ መልእክታት ናቸው። ጳው
ሎስ በ ነዚህ መልእክቶቹ የክርስቶስን ሰው የመሆን ምስጢር ገለጧል፤ በኤ
ፌሶን መልእክቱ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ምክቡርንና ከክርስቶስ ጋር ያለ
ውን ገንኙነትና ወሠረተ ሃይማኖትን ገለጠ አኖአል።

ሰለራቲኖው ኩፋለ ከሮማ የመጀመሪያ አሥራቱን በተፈታበት ጥቂት
ነፂ ነትን አግኝቶ ጎበረበተ ጊዜ በ63 አና በ68 ዓ.ም ጊዜ አንደተጻፉ
የሚገመቱ ገኖና 2ኛ ጢሞቲዎስቲቶንም ይይዛል፤ አ ነዚህም መልእክታት የጠ
ቅላላነት መልእክታት ይባላሉ ምክንያቱም የክህናትን ችግር የጠባቂዎቸንም
ኃላፊ ነት ከ ነተግባራቸው ገለጠው ይናገራሉና። የቀዱስ ጳውሎስ መልእክቶቸ
ሁሉ ገ ዓይ ነት ጠባይ አለ ቸው፤ ይኸውም የሚያመለክቱው በአንድ መንፈስ
ገለጭ ነት መጻፋቸውን ነው። ስለዚህ የአ ያንዳንዱን መልእክት ጠባይ ከመ
መርመር ይፉቅ ተመሳሳይ በመሆና ቸው የአንደኛውን መልእክት ጠባይ ከዚህ
አናሳ ያለን፤ ሁሉም በዚሁ ዓይ ነት ይ ሃዳሉና። ለአ ያንዳንዱ መልእክት
6 ክፍሉ አንዳለው አንገምታለን፤ ይኸውም አንደሚከ ተለው ነው።።

www.ethiopianorthodox.org

1. የመጀመሪያው ሰላምታ ነው፤ ከአያንዳንዱ መልእክታት ላይ ይነሰ ከሌሳውም ላይ ደግሞ ይብዛ አንዲ መልእክታቱን ሁሉ በሰላምታ ይጀ ምራቸዋል :: በመጀመሪያው የሰላምታ አገላለጥ ሰፊ ትምህርት ስለሚገኝበት የመሰብ፤ የማቅረብ፤ ወገንም የማድረግ ኃይል አለው፤ ስለዚህ በሰላምታ መጀመረን ተግባር አደረገው ::

. የሰላምታ ኢሰጣሙ :: ጸጋና ሰላም ለአናንተ ይሁን የሚል ነው፤ ይኸውም የዕብራውያን ሰላምና [illegible] ጸጋ በኮርስቶስ የመ[illegible] አንዲያንጉ የሚያነቃቃ ነው ::

2. ምሥጋና፤ ጳውሎስ ወደዋናው ርእስ ከመግባቱ ጣፊት ስለ ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ስጠታው አግዚአብሔርን ያመሰግናል ::

3. መሠረተ ሃይማኖቱ፤ ይኸም አንደሚጽፍበት ምክንያት ይለያዩ አንድ ዋና ነጥቡ በያዘው ርእስ ላይ አተኩሮ የርሱን ዓላማ አስፋፍቶ ይገልጣል :: አንዲሁም መልእክቱን ለመጻፍ የተነሣሣበትን ምክንያት ጠመከተል ሰፊ ትምህርት ይሰጣል ::

4. ተግባራዊ ትምህርት፤ የክርስቲያን ምግባር አንዴት መሆን አንደሚገባው ገለጠ ይጽፋል :: ይኸንም ርእስ ይጠቀምበት አንድ ካለፈው ትምህርት ጋር በአድ አንዳይሆን ትልቅ ጥንቃቄ በማድረግ ነው :: ሃይማኖትንና ምግባርን በማዋሃድ ያስተምራቸዋል ይኸው የሚሆንበት መልካም ምግባር የሃይማኖተኛ ሰው ውጤት አንደሆነ ገለጠ ያስረዳል ::

5. የግል ሰያቸ ሰላምታ፤ ይኸዉ የቅድስ ጳውሎስ የተለየ የፍቅረ መገለጫ ለአያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል ለሆኑ ይሰጥ የነበረ ነው፤ ይኸም አገላለጥ ሰፍር ያዊት ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደነበረች ከሚያስረዱት [illegible]

www.ethiopianorthodox.org

6. በዚያው በሐዋርያት ዘመን ብዙ የሐሰት መልእክት ይተላለፍና ብዙዎችንም ያሳስት ነበር፤ ስለዚህም ጳውሎስ መልእክቱ የርሱ ለመሆኑ ለማረጋገጥ፤ በእጁም ጻፈው መሆኑን ለመግለጥ ይጽፍ ነበር :: ይህንም ለማስረዳት ቅዱስ ጳውሎስ እንደማሕተም አድርጐ የሚጠቀምበት ቃል እንደሚከተለው ነበር፤ "ይኸን ሰላምታ በገዛ እጀ የጻፍኩት እኔ ጳውሎስ ነኝ፤ በእኔ መልእክት ሁሉ የሚገኘው ምልክት ይኸ ነው :: የምጽፈውም እንዲህ ነው፤ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን" / ተሰሎንቄ 3.17-18/ ይል ነበር ::

ሥ. - <u>ምዕራፍ 2 ወደ ሮሜ ሰዎች የተላከች መልእክት፤</u>

1. <u>ሀገሯ፤</u> ይኸች ሮም አሁን የኢጣሊያ ዋና ከተማ ናት በቀድመው ዘመን ግን የታሮቁት ዓለማት ሁሉ ርእስ ከተማ ነበረች፤ ክርስቶስ በተወለደበት ጊዜ ምዕራቡንና መሥሪቱን ዓለም የሚገዙ ነገሥታት የሚነግሱ በዚያች ከተማ ነበር፤ ስለዚህ የዓለም ከተማ ትባል ነበረች :: የሮም ግዛት ሰፊ በመሆኑ በየቅኝ አገር የሚኖረ ሕዝቦች ሁሉ ወደሮም እየገቡ ስለሚኖረ የሕዝቡ ብዛት መጠን አልነበረውም ::

የሆነ ሆኖ መደበኛ ቋንቋ ሆኖ ይነገር የነበረው ግሪክኛ ነበር፤ በዚህም ምክንያት ኤሌኖሮማይስ/ የግሪክና የሮም/ አጋዚዝ እየተባለ ይነገር ነበር :: የንጉሱ ነገሥት ከተማ.ብመሆኑ የልዩ ልዩ ሃይማኖት ሰዎችም ይገኙበት ነበር፤ በተለይ ግን አይሁድ ምኩራብ ሰርተው ሃይማኖታቸውን አጽንተው ብዙ አሕዛብ እየሰቡ ተምጠው ነበር ::

www.ethiopianorthodox.org

አንደሌላውም ሁሉ የክርስቲያን ሃይማኖት ፈጥኖ ወደ ሮም ገብቶ ነበር፤ ምክንያቱም ፤

1. ቅዱስ ጳውሎስ ከሮም ሃር ትልቅ ግንኙነት ካላቸው አገሮች አንደኤፌሶን፤ ቆሮንቶስ፤ ተሰሎንቄ አቲና ባሉት ከተማዎች ብዙ አስተምሮ ነቦርና ከዚያ ስምተው አምነው ስለ ሃዳና አይሁድንም አሕዛብንም ለመስበክ ስለ ቻሉ፤

2. ጠንጠቀስጢ ጊዜ በግፉ ፍላጐታቸው ጠኢየሩሳሌም ቀሰብስ በው ከነበረት ሮማዊያን አይሁድ ውስጥ የቅዱስ ጴጥሮስን [illegible] ኦርቶዶክስ አንዳቃሙ ይገ መታሉና ::

3. ቅዱስ ጴጥሮስ ገብቶ ራሱ በሰፊው ሰብክ ነበርና :: ቅዱስ ጳውሎስ በዚያ ብዙ ክርስቲያኖች መኖራቸውን ቤተ ክርስቲያንም ማቋቋማቸውን ሰምቶ የሰላምታ ቃሉና ምክር ተግሣጽ ትምህርት ያለበትን መልእክት ጻፈላቸው ::

2. የመልእክቲቱ ተቀባይቻች፤

ይኸች የጳውሎስ መልእክት ቦደ ሮሜ ሰያች መላኪና የጳውሎስም መልእክት መሆኗ የተረጋገጠ ነው፤ ነገር ግን ጥንትም ሆነ አሁንም ሰመ ረምረት አስቸጋሪ የሆኑ ነገሮች ቦውስጡ ይገኙበታል፤ ይኸውም የመጨረሻው ምዕራፍ በዚያን ጊዜ ያለተጻፈ በኋላ የተለጠፈ አንደሆነ በመገመት ነው ::

በዚህም ምዕራፍ የብዙ ሰቻች ስሞች ተጠቅሰ ስለሚገኝ ፤

1. በሮም ይህን ያህል ክርስቲያኖች በዚያን ጊዜ ይገኝ ነበ ርንን እንዴት ከማንስ ተማረ?

2. እነዚህስ ኮርስቲያኖች ቢኖረ ጳውሎስ እንዴት ለይቶ አወ ቃቸውና ስማቸውን እየጠራ ሊጸፍ ቻለ በማለት ነው ::

www.ethiopianorthodox.org

ምናልባት በሱ ሰብከት ከአመኑት ውስጥ ከኤፌሶን ኮ ተሰሎንቄ ፣ ከአንጾኪያ ከአቴን እሷ ለሱ የሃዱ ክርስቲያኖች ይሆኑን የሚለም ግምታዊ ጥያቄም አለ :: በእንዳንድ የእጅ ጽሑፎች በሆኑ ጥንታዊያን መጻሕፍት "ጎበ ሰብአ ሮሜ" የሚለውን ቃል አይጸፈትም ነበር፣ ይህንንም በመመለከት ጳውሎስ ይሸቸን መልእክት በሮሜ ላሉት ክርስቲያኖች ብቻ ሳይሆን በየትኛውም ሀገርና ቦታ የሚገኙ ክርስቲያኖች እንዲያነቧት የተጻፈች ናት፣ የመዐረሻው 16ኛው ምዕራፍ ግን በኋላ የተመረ ቀድመ ወደ ኤፌሶን ተልኮ የነበረ ነው ይላሉ ::

ይሸንም አስተያየት ሊያመጣ የቻልው ራሱ አየተገኘ በሰበከበት ከተማ ለሚገኙት ምዕመናን ሁሉ ከመልዮ ጋር ለሚያውቃቸው እንኪን የዚህን ያህል ሰም በመጥራት ሰላምታ አይጽፍም በማለት ነው ::

መልእክቷንስ የሚቀበሉ አይሁድ ክርስቲያኖች ናቸውን? ወይስ ከአራማዊያን ውስጥ ያመኑ ክርስቲያኖችን እንዳንደች ከአራማውያን ውስጥ ያመኑ ኮርስቲያኖች እንደሆኑ ይገምታሉ :: ሉሎች ደግሞ ከአይሁድ ውስጥ ያመኑ ክርስቲያኖች እንዲሆኑ ይናገራሉ :: አንደ ጳውሎስ አገላለጥ ግን በመልእክቲቱ መጀመሪያ ከአሕዛብ ውስጥ ለአመኑ ኮርስቲያን እንደሆነ ይገልጣል /1.5-7/ አንዲሁም/ በ1.13-15/ በመቀጠልም/በ1.13/ለ አሕዛብ እንዲሁ እሳለሁ አያለ ይናገራል :: እንዲሁም /በ15.14-16 ገልጠ ይናገራል/ :: ይሸን ሁሉ ስንመለከት በቀጥታ ከአሕዛብ ለአመኑ ክርስቲያኖች የጻፈው መሆኑን እንረዳለን ::

በሌላ በኩል ደግሞ የአይሁድን ሕግ ለሚያውቁ ይጽፍላቸዋል፣ ስለዚህም ናነአብር ሃምን አባትነት አያነሣ ከርሱም ዘር ክርስቶስ በስጋ እንደተወለደ ይጽፋል/9.5/ :: እንዲሁም/4.1፣2.1. 17-29 በሚገኙት ምዕራፍች አግባቤዎች ይሁዳዎች እንደሆኑ ይጠቁመናል ::እንዲሁም፣ ከሌሎች መልእክታቱ ይልቅ በዚህች መልእክት ላይ ስለ ብሉይ ኪዳን መላእክ ያስረዳል፣ ይጥቅሳል ሥርዓቱን ሁሉ ገልጠ ይናገራል ::

www.ethiopianorthodox.org

በነዚህ ማሰረጃዎች እንደምንረዳው ቤተ ክርስቲያኒ በሁለቱም ወገኖች የተቋቋመች ኑራለች፤ በዚህም ምክንያት በመካከላቸው ስምምነት አልነበረም፤ ሁለቱንም ወገን ለማግኘት ዓላማይ የሆነችውን ሰላምታና ትምህርት አስተላለፈላቸው :: መልእክታ የተጻፈች በግሪክኛ ነው፤ ይሽም ብዙያቹ ከአሕዛብ ወገን መሆናቸውን በዚያም ብዙያቹ ግሪክች እንደነበረ ይጠይቃል ::

3. <u>ወዴት፤ መቼ፤ ለምን እንደተጻፈች፤</u> ለሮሜ ሰዎች የተጻፈችላቸው መልእክት ቅዱስ ጳውሎስ በቆሮንቶስ አንድ ዓመት ከገ ወር ያህል ተቀምጠ ሰለ የጻፈው ነው :: ቅዱስ ጳውሎስ በዚያ ሲያስተምር [illegible] የሚረዱ የገንዘብ እርዳታ ከግሪክ ሕዝብ አወጣጥቶ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ሲነሣ ሲል ነው /ሮሜ 15.25-6/ :: ከኢየሩሳሌም ሰመለስ ወደ ሮም ሂደ እነርሱን እንደሚገብኝ አግረ መንገዱንም ወደ አስፖኝ ለመሄድ ዖኖት አንዳለው በዚሁ መልእክት በምእራፍ 15.28 ይናገራል :: ይሽንንም መልእክት የጻፈው በሦስተኛው ጠዋር ያዊ ገዛው ቦ58 ዓ.ም እንደሆነ ይገመታል የጻፈበትም ምክንያት በሮሜ ከአይሁድና ከአሕዛብ ውስጥ ክርስቲያን የሆኑት በሰርዓትና በባሕል ብዙ ጊዜ አይስማሙም ነበር፤ ወንጌል የምትሰብኩው ደግሞ ፍቅርን ሰላምን ነው :: በሮሜ የነበረ ክርስቲያኖች ግን ሁልጊዜ ክርክርን ጭቅጭቅን ያሳዩ ነበር፤ የዚህም ዜና ለቅዱስ ጳውሎስ በሰፊው ሰለ ደረሰው ቅዱስ ጳውሎስ ሁለቱን ወገን ለማስታረቅ ሲል ይሽችን መልእክት ጻፈ :: ከሁሉ በፊት ወንጌል የተጻፈችው ለአይሁድም ለአሕዛብም መሆኑን ለመግለጥ ነው/1.5-7/ ቀጥሎም ከርስቲያን የሆኑት ሁሉ በመንግሥት ላይ ያምጻሉ፤ ግብር አይገብሩም፤ የመ, ባል የሀሰት ወሬ እያወሩ ክርስቲያኖችን ከአሕዛብ ያጣሏቸው ነበርና በሥጋ፤ ለተሸመው ሁሉ በነፍስ ግን ለክርስቶስ መገዛት እን

www.ethiopianorthodox.org

ቢገባ ለዓለረጀ ጊዜ ጸፈ /13.1—7/: ደቀመዛሙርትንና ፋና ዓለሙ አድርጉ የጸረቡትን ሃይማኖት ነገ ቦሰዱ ፊዩ ተዘር ሲያለዝብ ከቀየ ቦኋላ ቦመጥረቧው ያቀረቦሩ ::/14.1—23/:: ቀና ዓለም ያደረገው ሁሉንም የአገዚአብሔርን መንግሥት በመስበክና ቦመጠየ የንዊርስ አገልጋይነን ፣ ጸድቆን ትረፉትን ቦመሥራት ፈቅርን አውነትን ቦመያዘ ነው አገሚ ቦፃለት ያሳረገገው /14.17/:: በዚህች መጽሐፍ ውስጥ ሰፊ የሃይማኖት ትምህርት አናረገበታለን ፣ ከርስቶስ ሰው አንደሆነ ስለአኛ መከረነ አንደተቀቦለ አናነ ፣ርሱን ለከትሰን ሠርነን ጸጋውን አንድነውርህ ቦሰሪው ያሳረገለች /ሮሜ.8.12—25/::

3. የመጽሐፉ ጽሑፍ አሰራነፋኛ ነት ፣ መህፃን መጽሐት ቀዳማ ጸሩሉስ አንደዓፈት ከጥንት ጀምሮ የአገልግሎ አሰራር ደንብና ፀሩስጥ ሰሳለጩ ነው ፣ ዓለት ጸሩ አስፈጅ ሐዋርያው ያን አቢያችን አገናዋ - ዱስ ፣ ጥው ለአንቦሳ ፣ ፖሊካርፖስ ፣ ሉሬ ንጠስ ዘሮሜ ቦመሳ አከያቻቸው በሰፊው ገለጠዋል::

የሰቦዋ ፣ ስክር ደገም ጸሐፊው አራቱን ጸጉሉስ ናሉ ገጠራናል /1.1./:: ሰንገሌ ትህርት የአመረጠና የጠራ ፈላስፋ በቀጥታ ቀርቡን የንጠት ፈሪክ የሔገደዋ ነው፣ ጋደሉ ቃሉና የአረጉት ነገረ አጫጫል ከሌሉች መጽሐፋች ጋር ሰለሚገናኝ የቅዱስ ጸፀ-ሉስ መጽሐት መሆኑን ይመስክራል::

የዕራን 3 1ኛ ቦደ ቆሮንቶስ ሰንች የተሳከች

1. <u>ሀገሯ</u>: ሮማች ቆሮንቶስ የጠቦሰች ከነገ ሰሞ ጥረና ታላቅ ከ

ነገ ነበረች ፣ ነገር ገን ሉኪያስ ሔዴስ በነቦሰ ቦሮግ የን ፍራ አለታ ቦ146 ዓመት ከክርስቶስ በፊት ነፃራ ታዋሳ ነበር ፣ በዚህም ሃገንያት ቦገሥት መቶ ዘመን ያህል ቆሮንቶስ የጠቦሰች ሰጭ ጠፍቶ ፀናር ነቦር ፣

www.ethiopianorthodox.org

ከክርስቶስ ልደት በፊት በ44 ዘመን አንደገና የሊዩስ ቄሣር የተባለው ንጉስ ነገሥት አደሶት፤ ይህችም በንግድ የታወቀች የሀብታሞች መናሸሪያ ነበረች፤ ለሚሠራቅና ለምዕራቡ ዓለም የንግድ መናሸሪያ በመሆኗ በልጽግናም ለሁሉ በመሆኑ የበለጸገች አገር ትባል ነበር ። በንግድ ምክንያት ከልዩ ልዩ አገሮች ከመጡት ሕዝቦች ጋር ኗሪው ሕዝብ በዝቶ ይታይ ነበር፤ በዚያን ጊዜ ከሰዱስት መቶ ሺህ አስከ 700 ሺህ ሕዝብ ይኖርባት እንደነበር ይገመታል ። በዚያም ከሚኖሩት ሕዝቦች በዝተው ይገኙ የነበረ ይሁዳዋች ፤ ሶሚዎች፤ ግሪኮች ነበሩ ። ሰው ሲበዛ ሁልጊዜ ኃጢአት መሠራት የታወቀ ነውና፤ ከዓለም ሁሉ ይልቅ በቆሮንቶስ የኃጢአት ዓይነት በዝቶ ይሠራ ነበር፤ በተለይም የዘሙት ሥራ በዝቶ ይሠራ ነበር ። ነገሩ ሁሉ እንዲህ በሆነበት ዘመን ቅዱስ ጳውሎስ ከአቴና ወደ ቆሮንቶስ መጣ/ የሐዋ. ሥራ 18. 1—18/። እርሱም ይሸን ያህል ኃጢያት በመሠራቱ ተጸጽቶ ስማዕያኑም በዝተው በአየ ጊዜ ቅዱስ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ብዙ ዘመናት ለመቀየት ፈለገ ። 1ኛ. ተሰሎንቄ 2.18/ ነገር ግን አንድ ዓመት ከገ ወራት ያህል እንደቀየ ሌሊት በራዕይ ክርስቶስ ተገልጠ ሰለነገረው / የሐዋ. ሥራ 18.9—11/ ቃዋር ያዊ ገዛውን ለመናገል ተነሣ ።

2. <u>መቼ ወዴት ለምን እንደተጻፈች፤</u> ቅድስ ጳውሎስ ቆሮንቶስን ለቀ ኢየሩሳሌም ገብቶ በግምት 2 ዓመት ቀይቶ እንደገና 3ኛ ጠዋርያዊ ገዛውን ቀጥሎ አያስተማረ ኤፌሶን ደረሰ፤ ከዚያም በዉት በማታ በጫደረገው ስብከት የእስክንድር ያው ሰው አጵሎስ የተባለው አይሁዳዊ አምኖ ተጠመቀ፤ ከተጠመቀም በኋላ የቅዱስ ጳውሎስ አረዳት ሆኖ ቆሮንቶስን ለመገብኘት ሄደ፤ ከዚያም እንደደረሰ በኮርስቶስ ስም ያስተምር ጀመር ።

www.ethiopianorthodox.org

የንግግር እቀድ ስለሚችል ብዙ ሰዎች በርሱ አምነው ቀጠመቁ፤ አርሱንም ብቻ እንደ መምህር አዉቁ፤ ብዙዎች ደግሞ ከቅዱስ ጸጥ ርኖስ ተመመቀጡ ሉንግዱ የመጡ ይሁዳዎች ሰብኢ ቅዱስ ሌዋዊነት ብቻ ነው እያሉ ይናገረ ነበር :: በቅዱስ ጳዉሎስ ስብከት ያመኑት ደግሞ ከቅዱስ ጳዉሎስ በቀር ሉሳ መምህር የለም ሲሉ ግማሽ ቹ ደግሞ ክርስቶስ ነው እንጂ እነዚህ ሁሉ ምኖ ቹ ናቸዉ ይጣሉት ቤተ ክርስቲያን ታሳቅ መሰያየት አደርጋ ስሉ ተበጣበጠች አጸዉሰ ይሽን ወፈ ልቅዱስ ጳዉሎስ ወደ ኤፌሶን ይዘሉት መጣ ::

ከዚህም በቀር ክርስቲያኖች ሉያደርጉት የጣይገባ ክግብ ሪንሰንት ሽጭ ናህ ቦራ በነኤጊሠራ ብለ ገለጠሉት ቅዱስ ጳዉሎስ ሌታገሰው አለቻለምና ይሽችን ጻፈ :: ከሁሉ ይልቅ የቆሮ ንቶስ ሰዎች ዝሙት አብዝተው ይሰረ እንደነበር ይሽች መልእክት ታስረዳለች :: ይሽችን መልእክት አጽፋለሁ አያለ ሲዘጋጁ ከቆሮ ንቶስ ም፩. 17-18/ :: አነርሱም የቤተ ክርስቲያንን ቸግር በጽሑፍ ያመጡ ናቸዉ ::

አነርሱም ያመጡት ሕዝቡ በታዘዙ ትእዛዝ በተሠራላቸዉ ሕግ ጣደር አለመቻላቸውን የሚገልጥ ነበር : /7-6/ :: ቅዱስ ጳዉሎስም ለአያንዳንዱ ጥያቄ መልስ አየሰጠ በተለየ ግን ከፍ አድራጊዎችን፤ ዝሙት ያበዙትን ሰዎች እንዲለዩዋቸው በሰፊው ገለጠ :: በ56 ዓመተ ምሕረት በኤፌሶን ጽፍ ከቆሮንቶስ ተልከው በመጡት በአስጢፋኖስ በፈረደናጥስ በአካይቶስ እጁ ላከው፤ ከሁሉም መልእክቶች ይልቅ በዚች መልእክት አስፈላጊውን ክርስ ቲያናዊ ትምህርትና አስቸጋሪ የሆኑትን ነገሮች ወስዷል ::

www.ethiopianorthodox.org

ከሁሉም ይልቅ ትንሣኤ ሙታን አንዳለ፤ ለጢስቱ የተሰየውን ሙሽ
ላት እንዳይገባ ክዝሙት መራቅ እንደሚገባ ዝሙት የሚሠራ መንግ
ሥተ ሰማያትን እንዳያይ፤ ከፋ አድራጊዎችን መለየት እንደሚገባ
አስፋፍቶ ጻፈ ::

3. <u>የመልእክቲቱ አውነተኛነት፤</u>

ገና የቆሮንቶስ መልእክት በቅዱስ ጳውሎስ እንደ ተጻፈች የተገ
ለጠ ነው፤ ለዚህም የውጭና የውስጥ አስረጅ አለው ፤

ገና የውጭ አስረጅ ተለምናጠሱ ዘርም ወደ ቆሮንቶስ ቤጻፈው
መልእክቱ ቅዱስ ጳውሎስ ይኸችን መልእክት እንደጻፈ ይገ
ልጠለናል፤ ሌሎቹም የቤቱ ክርስቲያን አባቶች ሁሉ ብሱ
ፊው ያስረዳሉ ::

2ና. የውስጥ ምስክር ጸሐፊው እየመሰለሰ ስሙን ጳውሎስ ይሉል
/1.16-21፤ 1.12፤ 3.4-22/ :: የዐረፍተ ነገሩ
አሰካክና የኃይለ ቃሉ አጠቃቀም በሰፊው ቅዱስ ጳውሎስ
እንደጻፈው ይመሰክራል ::

www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ 4 2ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች የተላከች

1. <u>ወዴት መቼ ለምን እንደ ተጻፈች፤</u> የመጀመሪያቱ ወደ ቆሮንቶስ የተላከች ቅዱስ ጳውሎስ በመንገድ ሳለ በመጀመሪያ መልእክቱ ቢቆሮንቶስ ሰዎች እንደ ተጠ ቀሰው የጳውሎስን ትምህርት እንደ ተቀበሉ በነገረው ጊዜ በከባድ ኃጢያት የወደ ቁትን ለይ ተው ገሣጽ ም ንስሐ ገብ ተው በቁና ው መንገድ እንደሚሄዱ በስማ ጊዜ ቅዱስ ጳውሎስ ከባድ መልእክት በመጻ ፉና ሰዎቹን በማሰዘኑ /7:8-9/ : በእነዚህ ሁሉ ምክንያት ተጸጽቶ የምሥጋና ቃልንና ምክርን ጻፈ፤ ነገር ግን በመካከላቸው አይሁዳዊና አረማዊ ተለያይ ተው እንደሚነቃቀፉ ንስሐም እንዳልገቡ/12.21 አይ ሁዳዊውም በኮርስቶስ እንደሚምካ /10.7-16፤4፤22/ :: በስማ ገዜ ይህን [illegible] ጳፈ :: መልእክት በ57 ዓ.ም ገደማ ተጸፈች የተጻፈችበትም አገር ፈለጵስ ዩስ እንደሆነ ይገመታል ::

2. <u>የመልእክቲቱ እውነተኛነት፤</u> ይህች 2ኛ የቆሮንቶስ መልእክት እር ግጠኛ ቅዱስ ጳውሎስ የጻፋት መሆኗን የውስጥና የውጭ ምስክር ያስ ረዳል :: ማለት የውጭ መስክር ቀሌምናጠስ ዘሮሜ የመጀመሪያ መል እክት በሆነው መጻሕፍ መስክሯል፤ ፖሊካርፖስም ወደ ፊልጵስዩስ በሳከው መልእክቱ፤ ሄሬኒቃስም፤ እንዲሁ ብዙ ሌሎች ሊቃውንት በሰፊው አስረድተዋል ::

የውስጥ ምስክር ራሱ ጸሐፊው ስሙን ጳውሎስ ብሎ አስረድ ቷል :: ደግሞም የኃይለ ቃሉና የምስጢር አገላለጡም ከሌሎች የጳ ውሎስ መልእክቶች ጋር ስለሚመሳሰል ጸሐፊው ጳውሎስ እንደሆነ ያስ ረዳል በ ተለይም ከሮሜና በገላትያ መልእክቶች ጋር ይመሳሰላል :: ከዚህም በላይ የቅዱስ ጳውሎስ አይደለም የሚል ተቃዋሚ ባለ መነሳቱ አይጠራጠርም ::

www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ 5 ወደ ገላትያ ሰዎች የተላከች

1. ሀገሯ፤ ይህች ገላትያ የተባለች አገር በ2ት ወንዞች ማጉጌፅያስና አሊ የስ በተሰሉት መካከል የምትገኝ አገር ናት ዛሬ ግን የቱርክ መናገሻ ከተማ አንካራ የሚባለው የሚገኝበት ናት :: ቀድም ታላቅ አውራጃ ሆኖ በውስጧ ጲስድያ፤ ኢስሙር ያ ሊያአን ያ ፍርገያ ቲልቀያ የቴሌሎትን ወረ ዳዎች ሁሉ ይዛ ነበር :: ቅዱስ ጳውሎስ በሁለተኛው ሐዋርያዊ ጉዞው በግምት በ52 ዓ.ም አያስተማረ ስልዋኖስንና ጢሞቴዎስን አስከትሉ ከዚህች አገር ደረሰ በዚች አገር ብዙ ጊዜ ሊያሰልፍ አሰፈ ቀደም ነበር፤ ነገር ግን [illegible] ጥቂት ጊዜያቶች ስለቀየ አስ ተምሯል ::/ገላትያ 4:13/ በዚች በጥቂት ጊዜ በስብከቱ ብዙ ሰዎችን እጁ አደርጊል :: አንዲያውም በመካከላችው ፍጽም መግ ባባትና መተሳሰብ እንደ ነበራቸው እራሱ ቅዱስ ጳውሎስ መስክሮለ ቸዋል/ገላትያ 4:15/ ከ3ት ዓመት በኃላ ይህችን ቤተ ክርስ ቲያን ለመጎብኘት ቅዱስ ጳውሎስ ጓናውን የሐዋርያዊ ጉዞ እንደ ጀመረ ገላትያ ደረሰ፤ ከ3ት ዓመት በፊት ጀምሮት የነበረውን ትምህርቱን በዚህ በ2ኛው ጉብኝቱ አጽንቶ አስፋፍቶ አስተማራቸው ::

2ኛ. መቼ ወዴት ለምን እንደተጻፈች፤ ቅዱስ ጳውሎስ ከጻፋቸው መልእ ክቶች መቼ ወዴት እንደተጻፈች የምታስችግር ይህች ወደ ገላትያ የተላከች መልእክት ናት :: ብዙዎች የትርጓሜ ሰዎች ቅዱስ ጳው ሎስ በኤፌሶን ሳለ ጻፈ ይላሉ፤ ሌሎች ደግሞ ኤፌሶንን ለቅቆ ከሄደ በኃላ እንደጻፈት ይናገራሉ :: የሚመስለው አስተያየት ግን ወዲያው እነርሱን አስተምሮ ወደ ኤፌሶን ሲደርስ ቢጽ ሐሳውያን በአገረ ተተክተው የገላትያን ክርስቲያኖች እንደበጠበጧቸው ሰምቶ ልዋል ልደር ሳይል በ57 ዓ.ም እንደ ጻፈት ነው ::

www.ethiopianorthodox.org

በመሳ የገላትያ ሰያቸ ከወንጌል ትምህርት እንደወጡ ከክርስትናው ሃይማኖት እንደ ተናወጡ ፭ኛው ምዕራፍ በሰፊው ያስረዳል :: የተጻፈበትም ምክንያት ቢጽ ሠሪ ያን የጳውሎስን መራቅ ሰምተው ብትሠመቁ የሙሴን ሕግ ካልጠበቃቸሁና ካልተገዘራችሁ ምን ይረባችኋል ምንስ ይጠቅማችኋል፤ ቅዱስ ጳውሎስ የምትሉት አስተማሪ ሾመቱን ኮሰው አንድ ከአግዚአብሔር አላገኘውም ለምን ትሰሙት አላችሁ ይሏቸው ነበርና ለማጽናናት ነው :: ይህም የቢጽ ሠሳያውያን ትምህርት በቆሮንቶስ እንደ ነበረው ያለ ነው፤ ምክንያቱም ይህች መልእክትና የቆሮንቶስ 2ኛ ዩት መልእክት በጣም ይመሳሰሉ ናቸው ::

3ኛ. <u>የመልእክቷ አውነተኛነት፤</u> ይህችን መልእክት አራቱ ቅዱስ ጳውሎስ እንደ ጻፈት የውጭ ምስክር ፖሊካርፖስና አግናጥዩስ በጽሑፍ በሰፊው አስረድተዋል፤ ይህንም የመሰለ ብዙ አስረድ አለ :: ከዚህ የበለጠ ግን የውስጥ አስረድ ይገኛል ይኸውም ኣራቱ ቅዱስ ጳውሎስ እንደጻፈው 2 ጊዜ ይመሰክራል ::/1.1፤5.2/ ከዚህም ጋር በሌላ ያች መልእክቶቻችና በጠቅላይ ቅዱስ ጳውሎስ ከሠራ :: ቸው ሥራ ያች ስለሚጠቅሰ ሰመልእክቶቹ ሁሉ የሚገኙ ኃይለ ቃሎችና የአይፋት ነገሮች አጣጣል ቅዱስ ጳውሎስ እንደጻፈው ያመሰክራል ::

<u>ምዕራፍ ፩ በጳውሎስ የመጀመሪያ አሠራት ጊዜ የተጻፈ መልእክታት</u>

1. <u>ወቄትና መቼ እንደ ተጻፈ፤</u>

ወደ ኤፌሶን፤ ወደ ፊልጵስዩስ፤ ወደ ቶሳስ የሰና ወደ ፊልሞና የተሳኩ መልእክታት የተለየ አንድ ክፍል አንጻላቸው ሁኖ ይነገራል፤

www.ethiopianorthodox.org

ምክንያቱም አንድ ሓይነት ዐይም የሆለ የሆነ ምኵን ያት ያገናኛ ቸዋለ ስለዚህ በአሥር ቤት አንደ ተጻፊ ያስገንዝባሉ ። ይኸም ያገና ኛ ቸዋለ የተባለው ምልክት ብዙስጣ ቸው የሚገኙው የሚከ ተለው ኃይለ ቃል ነው/ኤፌ. 3.1፣4.1.6—20፣ ፊ፣ጳ.1.7፣13.14ግ7፣ ቀላስ 4.18 ፊልሞና 1/ ። እነዚህ መልእክታት አንድ ዓይነት ግንኙነት አላቸው አንበል፣ በአንድ በታም አንደ ተጻፊ ይገመ ት አንድ ሰው ሁለት ነገሮች ይገኝባቸዋለ ፣ እነ ዚህም አንደኛ በአሥሩ ቤት ይጻፊ ይባለ አንድ በታው ወዴት ነው? ሁለተኛው ግአንድ በታ ይጻፊ አንበለ አንድ ቁደም ተከ ተለ ቸውስ አንዴት ነው ማን ቀደም ተጻፈ? ቀጥሎስ የመጨረሻውስ ማንኛው ነው? ቀዳሬለ ነው ።

ስለ መጀመሪያው ጥያቄ የቀደሙ የቤተ ክርስቲያን አባቶች አንደ ተቀበሉት የሚገመ ተው እነዚህ መልእክታት በሮም አንደ ተጻፊ ነው፣ ይኸንም አንደነ የሐንስ አፈወቅ ያሉ አባቶች በግልጥ መስክ ረዋለ/ወደኤፌ መልእክት መቅድም፣ ኤሮኒሞስ ወደ ኤፌሶን /መልእክት፣ ቴያ ደረቸስም/ ። ይኸን ሐሳብም ብዙያቸ የትርጓሜ ሊቃውንት ይስማ ሙበታል ።

አንዲሁም ጥቂቶቸ የትርጓሜ ሊቃውንት ጳውሎስ በ ቂሣር ያ ለ2 ዓመታት ታሥሮ ሳለ አንደጻፊቸው የሚናገሩ አሉ ለዚህም ማስ ረጃ አደርገው የሚያቀርቡት የፊልሞና መልእክት ለመጻፍ ምክንያት የሆነው አናሲሞስ በ ቂሣርያ ጳውሎስ ስለሚገኝ ከ ቀላስያስ ተነሥቶ ሔደ አማላጁነት አንደጠየቀው በመገመት ነው ። ሮም ድረስ ሔደ አማላጁነት ሊጠይቀው አይቸልም ነበር፣ ማለት ገኖ አገሩ ረቅ ስለሆነ ከዚያ ድረስ የሚሄደበት መገናኛው ያስቸገረ ናል፣ ሁለ ተኛም ብዙ ሕዝብ ባለበት ከ ተማ ጳውሎስን ፈልጉ ለማግኘት አስ ቸጋሪ ነበርና በ ቂሣርያ በቀርቡ ስላለለት ሔደ አማላጁነት ጠየ ቀው በዚያም ተጻፊ በሚለት ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

ይሽን አስተሳሰብ ግን በተቃራኒ የሚመለሱ አሉ፣ አሮሌሙስ ቀዲ ታውን ግንዘብ ከአጠፋ በኋላ ጌታው በሚገኝቡት አቀራቢያ ሊኖር አይቸ ልም፣ ወደ ቂሣርያ ሊሔዱ አይችልም፣ ስግዱ ርቀ መሬዱ መሰወር መጥፋት አለሰትኖ ውደርም ሔደ ይሆናል፣ ከዚያ ከሄደም ዘንድ ሰላ ጳውሎስ ስም ቱ ክአለሰት ድረስ ሂደ አማላጁነትን ጠይቀት ይሆናል፣ ስለዚህ እነዚህ መለ አክቶች በሮም መጻፍ ግድ አለባቸው ይሳሉ ::

ከዚህም በቀር ብዙ ሊቃውንት በሮም መጻፋቸውን እየተራዱ ሊያያዝ የመጣ ስለሆነ በሮም መጻፋቸውን ያጸድቃል :: ጸውሰጣቸውም ያለው መረጃ /ኤፌ.6.19—2፣ፊልጵ 1.12—13 ቀሳስ 4.3፣4/ የዚያን ጊዜ ሁኔታ በገለጸ በሰኒያበረጉ ዘንም መጻፋቸውን ያጸድቃሉ :: ቀ. ጳውሎስ በሮም ታሥሮ በተከራየው ቤት እንግዳ የመቀበል የመስበክ የአጻፍ ነጻነት እንደነበረው ሉቃስ ገልጠልናል/ የሐ.ሥራ 28.16፣ቁ ሣርያ ግን የነበረው ነፃነት ምን ያህል እንደነበረ ስለማይታወቅ በዚያ ሊሆን አለመቻሉን ያረጋገጠል ::

ሁለተኛው ጥያቄ ደግሞ ስለ መልእክታቱ ቀደም ተከተለ ማወቅ ነው ይሽም የትርጓሜ ሰዎችን አስቸግሮ ይገኛል :: የሚታመነው ግን ኤፌሰን ቆላስይስ ፊልሞና አንዱ ጊዜ የተጻፉ መሆናቸውን በአንዱ ግድም መሳካ ቸውን ነው፣ ይሽውም /ኤፌሰን 6.21—22 ቀሳስ 4.7—9/ በሚገለ ጠው ልንረዳ እንችላለን ግን ከፊልጵስዩስ በፊት ወይም በኋላ መሆኑን አያስረዳም :: የፊልጵስዩስ መልእክት በመጨረሻ ጊዜ እንደተጻፉት የሚ ገመቱ የሚሰጡት ምክንያት ጌቱን ቀድሞ ጽፍ ከላከ በኋላ የፊልጵስዩስ ሰዎች እስኪያውቁትና መልእክት እስኪልኩለት ጊዜ ጠብቆ ቀይቶ መልእክ ታንም እስይዘ ሰጌታል :: ይሽን የሚደገፍ ሌላው ማስረጃ ደግሞ አርስ ጠርከስ የተባለው የጳውሎስ ረዳት በሮም አሥራት ያለተለየው / የሐ.ሥራ 27.2/በ ቀሳስ የስ /3.10—14/በፊልሞናም /24/ስሙ የተገለጠ ሲሆን ከጳውሎስም ያለተለየ መሆኑ ሲገለጥ በፊልጵስዩስ መልእክት ግን ስሙ አለ ተጠራም ይሽን በመላሱ

www.ethiopianorthodox.org

መልእክት

በመጨረሻ የተጻፈች መሆኗን ሌሎች ጉዳዮች ግን ቀድመው የተጻፈ እንደሆኑ ይገምታሉ ::

ምዕራፍ 7 የጳውሎስ መልእክት ወደ ኤፌሶን ሰዎች

1. **የመልእክቲቱ ተቀባዮች፤** ወደ ኤፌሶን ሰዎች ስንደ ተላከችው መልእክት ያለ ተቀባይዋ ማን እንደሆነ ለማወቅ ያስችግረ መልእክት ከጳውሎስ መልእክታት ውስጥ አንድም አልተገኘም :: ይኸን ችግር ሊያመጡ የቻሉትም የሚከተሉት ምክንያቶች ናቸው 1.ከሐዋ.ሥራ /18.19፤19.8.13-16/ እንደምንረዳው በኤፌሶን ብዙ ይሁዳዊች ይገኙ ነበር :: ስለዚህ የመልእክቲቱ ተቀባይ እነርሱ ሳይሆኑ አይቀርም የሚል ግምት አለ፤ ምክንያቱም ወደ ነርሱም እንደተላከ የሚጠቁም ብዙ ነገር ይገናኛል :/2.11-19፤3.1/

2. እንዲሁም በሐ.ሥራ ጳውሎስ በኤፌሶን ከ2 ዓመት በላይ እንደቆየ የታወቀ ነው/19.8.10/ :: ስለዚህ በዚያች ከተማ በቁጥር ብዙ የሆኑ አማኞቻች የተለዩም የጳውሎስ ወዳጆች እንደነበረት ልንጠራጠር እንችልም እንዲሁም ይኸች መልእክት በተጻፈች ጊዜ እንደ ጢሞቴዎስ እንደ አርስጠርኮስ ያሉ ታማኞች ከቀ.ጳውሎስ ያልተለዩ የትረፋት አበጋዞች ነበረ/የሐ.ሥራ 19?29፤ 1 ቆሮ 4.17/ :: ይህ ሁሉ ከሆነ ዘንድ እንዴት ከብዙዎቹ ለነርሱ እንኪን ከጳውሎስም ከሁለቱ ረዳቶቹ ዘንድ የተለየ ሰላምታ የተጻፈለት ስሙም የተነሣ ሰው የለም ይህ ሁሉ ሁኔቴ በብዙዎች ዘንድ አስገራሚ ሁኖ ተገኝቷል፤ በሌሎች መልእክቱ በተናገረው መልክ በተጻፈላቸው ሰዎች እንደሚገኙ በጣም ግልጥ ነው :: እንግዲያውስ በዚህች መልእክት የበለጠ ሲሆን ይገባው ነበር፤ስለዚህ እንዲህ ሊሆን የቻለው የመልእክቲቱ ተቀባይ ማን ቢሆን ነው በማለት መለስ የሌለው ጥያቄ ተቃጥቶ ይገኛል ::

www.ethiopianorthodox.org

3. ጳውሎስ በኤፌሶን ለሚገኙት ወዳጁ ሰላምታ አስመጻፉ ብቻ ሳይሆን አነርሱም እንደማያውቁት እርሱም እንደማያውቃቸው ኮሎሳ ሰሙተው እንዳሙኑ የሚገልጥ ዐረፍተ ነገር ይገኝለታል/3 2-4/ ::

4. ይህን ከዚህ በላይ ያተትነውን በመከተል መልእክቲቱም ለኤፌሶን ሰዎች መላኳን ያጠራጥራል፤ ይህውም ከዚህ በታች የሚገኘውን አስረድ በመ መርከዝ ነው ሀ. ጥንታዊያን የእጁ ጽሑፎች የባቲካን፤ የአስከን ድር ያም ኮዴክስ ላሉቸም በብዙ የሚቆጠረ የቡዛ የእጁ ጽሑፎችም፤ ከኤፌሶን መልእክት በመጀመሪያው ምዕራፍ በገፍው ቁጥር ላይ በኤ ፌሶን ለሚገኙ የሚል ስም አልነበረበትም፤ ይህ ቃል በጠም ቀይ ተው ከተጻፈት ኮዴክሶች በጭማሪ የገባ እንጁ ::

ለ. ታላቁ ባስልዮስ በዚህች መልእክት እጁ ጽሑፉ በኤፌሶን የሚል ቃል አልነበረበትም/ሲል መስክሮ ጽፍል ይህን በመሰለው ምክንያት ወደ ኤፌሶን የተላከቸው የጳውሎስ መልእክት ወደዜትኛዋ ቤተ ክርስ ቴያን እንደተላከች ግልጥ ሳለመሆኑ ብዙዎች ተቸግረው ሐሳባቸውን ሁሉ በጽሑፍ የገለጡበት ርእስ ነበር :: የኋላ የትርጉም ሊቃው ንትም ይህንኑ በመከተል ይህች መልእክት ወደ ኤፌሶን ቤተ ክርስ መላኳን ተቃውመዋል ::ብዙዎች እንደሚሉት ይህች መልእክት ወደ ሎዶ ቅያ ተልካ የነበረች ናት :: የሆነው ሁኖ በሚቀጥለው አስተያዩት ችግረ ይጠያለላል 1. ወደ ሎዶቅያ የተላከች ከሆነች ለቆላስያስ ሰዎች የተላከውን ሰላምታ ወደ ሎዶቅያ እንዲያስተላልፈለት ባል ጻፈም ነበር ::/ቆላስ. 4.15/፤ 2ቱም መልእክቶች በቲኪቆስ እጁ ወደ ታናሹ እስያ የተጻፉ ናቸውና ::

3. ጳውሎስ ለቆላስያስ ሰዎች የተላከችውን መልእክት ለሎዶቅያ ሰዎች እንዲያነቡ ለሎዶቅያም የተደፋችውን ለቆላሰይስ እንዱያነው :: እያዘም ነበር ይህን ሁሉ ችግር በመመልከት ደግሞ ይህች መልእክት ለኤፌሶንንም ሰዎች ለሎዶቅያም ሰዎች በተለይ የተላከች አይደለችም

www.ethiopianorthodox.org

አንቺቲኩ አስያ ለተባሉት ሁሉ ተዘዋውራ የምትደርስ በሁሉም ዘንድ የም
ትነበብ አደርጉ አንዳጸፈትና እንደሳካት ይገምታሉ :: ቅዱስ ጳውሎስ ታሥሮ
ወደሮም ሊሔድ በቲቂስ እጁ ለቆሳስይስ፣ ለፊልጵስዩ ቤተ ክርስቲያን ሲጽ
ፍና ሲልክ በዚያ አካባቢ በሚገኙ አብያት ክርስቲያናት በጠቅላላው እንዱ
ትደርስ አስቦ ይህችን መልእክት የላካት ተሆናለች በማለት ይደመድማሉ ::
ለዚህም ሁሉ ክፍተኛ ንቁናቂ የነበራት በሰውም ብዛት በንግዱም ሰፋት ኤፌ
ሶን ስለሆነች የኃላ ሰዎች የኤፌሶን መልእክት በማለት አስገብተውበት ነው
እንጁ ይላሉ ::

2 የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን

ኤፌሶን የተባለችው ከተማ ጥንታዊ ሥልጣኔ ያላት ከተማ ነበረች፣ ትገኝ
የነበረው ለአስያ በምዕራቡ ክፍል ነው፣ ለንግዱ ተስማሚ በመሆኗና ጠቅላይ
ገዥም ስለሚቀመጥበት ክታማኖ ክፍ ያለች ነበረች፣ ብዙ ልዩ ልዩ ሕዝቦች
ስለሚኖረባትም የግሪኩ የአስያቲኩ ዕውቀት ተበራክቶባት ነበር፣ በዚህም
ምክንያት የአስያ ብርሃን ተባለ ተሰይማ ነበረች፣ በዚህች ከተማ ሕዝቡ
በዘቶ በሚማናት ተለያይቶ ይኖር ነበር :: ብዙ መስጊደችም /ምኩራቦችም/
ይገኝበት ነበር :: ከዚያውም ውስጥ ስመጥሩ የሆነው ሥራው 200 ዓመት
የፈጀ የአሮጌሚስ ምኩራብ ይገኝ ነበር ይህም ሥራ በመላ አስያውያን ሁሉ
ገንዘብ አውጥተው የተሰራ ነበር ከምኩራቡ ሥራ የበለጠ ደግሞ በብዙ ርቀት
የተሠራ የአርጢምስ ጠርሳት/ጣኦት/ በውጤ ይገኝ ነበር :: ከዚህም ጣዖታት
ሥራ በጣም አስደናቂ ሁኖ ችአንጧት ከድንጋይ፣ ከዝሆን ጥርስ ከሌላም
ይህን ከመሰለ የተሠራ እንደሆነ ለመለየት አይቻልም ነበር :: ጠበብቱም
ግሪኮችና አስያውያን ነበሩ :: ቅዱስ ጳውሎስ በመጀመሪያውጊዜ አየሰበከ
በግምት በ54 ዓ.ም ከቆሮንቶስ ወደ ኤፌሶን በሁለተኛው ጉዋዞ ያቺ ገዛው
መጨረሻ ላይ ደረሰ/የሐዋ. ሥራ 18.19-21/ ::

በዚህ ጊዜ እውሉስ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሻገር ስለ አሰበ በዚያ
ብዙ ጊዜ ሊቀይ አልፈቀደም ነበር :: ነገር ግን በ3ኛው ጉዞው እንደገና
ወደ ኤፌሶን መጣ እንደለመዱ ወደ ምኩራብ ገብቶ ::

www.ethiopianorthodox.org

ከዚያም ሕዝቡ ሁሉ በማከበር ትምህርቱን ሲቀበሉት ታምራትም ሲያሳያቸው ወንጌ
ልን አክብረው ተቀበሉ/ የሐ.ሥራ 19.11/ ይህን ትምህርትና ታምራት በቁመ
ለከቱ ጊዜ ጠንቋዮችና ከከብ ቀጣሪዎች የነርሱ ሥራ ኮንቶ እንደሆነ ተረ
ድተው ቅዱስ ጳውሎስን ሊጣሉት መጡ፤ እነዚህ ብቻ ሳይሆኑ ብአስተ አየቀረጽ
ይሸጡ የነበር ግንዳቸው ስለቀመጣቸው፤ ለጣዖታትም ስለት ይገባ የነበረው
ስለተቋረጠባቸው በዚህም ምክንያት ገቢ ያገኙ የነበረ ሠሌ ቅዱስ ጳውሎ
ስን በጥብቅ ይጣሉት ጀመር፤ እንዲያውም ሉገሉት ፈለጉ በከርስቲያኖች
እርዳታ አምልጠ ወደ መቄዶንያ ሄደ፤ ስለዚህም በኤፌሶን ክልከላ ጋር
ተጣለሁ ይላል/1ኛ ቆሮ.15.32/ ብዙ ዘመን ከቀየ በኋላ መልእክቱ
ለኤፌሶን ሰዎች ጻፈላቸው ::

3. <u>መቼ ወዴት ለምን እንደተጻፈች፤</u> ቅዱስ ጳውሎስ በልዩ ልዩ ሰዎች ምቀ
ኝነትና ተንኮል ምክንያት ኤፌሶን ከለቀቀ በኋላ ስለ ኤፌሶን ሰዎች
ልዩ ልዩ ሰም ሲያወጣላቸው ይሰማ ነበር :: ይኸን ሰማቸውና በከ
ርከቶስ ስም እንዲያዩሱት 2ኛም ከተማዋ ትልቅ ከመሆኗ የተነሳ
የዘሙት ነገር ይምቀ ይስማበት ነበርና ጋብቻ ቅዱስ ምዕጢር ዘሙት
ግን አርኩሶት እንደሆነ ጋብቻን በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን
እየመሰለ ጻፈ፤ በዚህም አገላለጥ ችሌሎች መልእክቶች ያልተገለጠ
የጋብቻ ምዕጢር ብሉ የሚነገርው ተጽፍ ይገኛል /5.32/ ::
የተላፈበትም አገር ሮም ነው ያሥሮ ሳለ በግምት በ63 ዓ.ም
ነው ::

4. <u>የመልእክቲቱ አውነተኛነት፤</u> ይህችን መልእክት ቅዱስ ጳውሎስ
እንደጻፉት ልዩ ልዩ ምስክሮች አናገኛለን እነዚህም የውጭ ምስ
ክር የውስጥ ምስክር በማለት ይከፈላሉ የውጭ ምስክር የቤተ ክር
ስቲያን አቦቶች ናቸው እነዚህ ሁሉ በጽሑፍ አስረድተዋል ::

www.ethiopianorthodox.org

የውስጥ ምስክር እራሱ ቅዱስ ጳውሎስ ስሙን በመጥራት ይመሰክራል /ኤፌሰን/ም.1ቁ 1ም.6ቁ 5/ :: ከዚህም ሌላ ኃይለ ቃሉ ዐረፍተ ነገሩ፣ የጽሕፈት መጀመሪያና መጨረሻ ቃሉ ቅዱስ ጳውሎስ እንደጻፉት በሰፊው ያስረዳሉ ::

ምዕራፍ 8 ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች የተሰኪች፣

1. ሀገሯ ፣ ፊልጵስዩስ የተባለችው ከተማ በመቄዶንያ አውራጃ የምትገኝና፣ የታላቁ እስክንድር አባት ፊልጵስ ስለ መሠረታት በፊልጵስ ፊልጵስዩስ ተባለች :: በዚች አገር መጀመሪያ ቅዱስ ጳውሎስ በ52 ዓመተ .ም በሁለተኛው ሰዋር ያቂ ጉዞው ደረሰ በዚች ከተማ የሚኖሩ አይሁድ በቁጥር ያነሱ በመሆና ቸው እንደሌሎች ትልቅ ምኩራብ አልሠሩም ነበር :: ይሁን እንጂ በያሉበት የጸሎት ቤት እየሠሩ የሚጸልዩ ደጋግ ይሁዳዎች ነበሩ፣ ቅዱስ ጳውሎስም እነርሱን እረፈለገ ይሰብክ ነበር :: የቅዱስ ጳውሎስን ስብከት በመጀመሪያ በፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን ስደትና ፈተና ደረሰባት 2ኛ. ቆሮ 8. 1-7. ፊልጵስዩስ 1. 28-30/ ::

በ3ተኛው ሰዋር ያቂ ጉዞው እንደገና ይህችን ቤተ ክርስቲያን ቅ. ጳውሎስ እንደጎበኘ ይታሰብላል፣ ይኸውም በግምት በ58 ዓመተ ከክርስቶስ በኋላ መሆኑ ነው፣ /የሐ.ሥራ 20.1-6 በሮማ ታሥሮ ከተፈታ በኋላ ወደ መቄዶንያ ሲሄድ ኤፌሰን እንዲቆይ ተገደደ በ63 ከክርስቶስ በኋላ የፊልጵስዩን ቤተ ክርስቲያንን ጎበኘ /1ኛ ጢሞ.1.3/ ይህች ቤተ ክርስቲያን በቅዱስ ጳውሎስ ስብከት ድርጅታ ሰለነበር ብዙ ክርስቲያናዊ ተግባር ይፈጽምባት ነበር እግናጥዩስ ዮጥው ለእንበሳ ታሰሮ ወደ ሮም ሲሄድ በዓዩ ጊዜ ሳይፈራ በሰልፍና በክብር እንደተቀበሉት ወደ አዘሚርና ቤተ ክርስቲያንም እደሸኙት ራሱ በጻፈው መልእክቱ እናገኘዋለን ::

www.ethiopianorthodox.org

2ኛ. <u>መቼ፣ ዐዴት፣ ስለምን እንደ ተጻፈች፣</u> ወደ ፊልጵስዩስ የተጻፈችው መልእክት መጀመሪያ ቅዱስ ጳውሎስ ሮም ታሥሮ በ ነበረበት ጊዜ በ63 ዓ.ም ሮም ላይ ነው። የተጻፈበትም ምክንያት ኤጳፍሪ ስ የተባለው የፊልጵዩስ ቤተ ክርስቲያን አባል ወይም ጠባቂ የሆነ የፊልጵ ስዩስ ሕዝቦች ስለ አሰረኛው ስለ ጳውሎስ ያወጡትን አስተዋጽኦ ይዞ ወደ ሮም ሄደና ለቅዱስ ጳውሎስ አስረክቦ በፍጽም ስጫቱ ወንጌልን ቢያስተምር በጥብቅ ታመመ ይህም ነገር ስፊልጵስዩስ የሚገኙ ክር ስቲያን አሳዘናቸው ነበር፣ ከዚህ የተነሣ ሕዝቡ በሰማ ጊዜ ራሱ ወደ ነርሱ ለመሔድ ቋምጥ ጠበብ አደረገ። ይህ ምቹ ጊዜ ለቅዱስ ጳውሎስ ገጥሞት ስለ አደረጉለት አስተዋጽኦና ስለ ሃይማኖታቸው ጽንዓት ምስጋናውን ለመግለጥ ጻፈ። በእርግጥም ምዕመናኑን የሚ ያስደስት መልእክት ነበር፣ እንዲሁም የነርሱንና የእርሱን ፍቅር የሚገልጥ ምክርን አዘል የሆነ መልእክት ጻፈላቸው። ከዚያ አያይዘን ግን ሌላም ልዩ ልዩ አርእስት ዳሰብትን ጻፈ፣ ለም ሳሌ የወንጌል ትምህርት በ ነሱ ላይ እንዴት እንደ ተስፋፋ በማ ረጋገጥ ከዚህም አያይዞ ስለ ደስታ ስለ ሰላም ይገልጣል።

ከዚህም በኋላ አንድ ጉድለት ስለ አለባቸው እንዲያ ረሙ ይመክራቸዋል፣ ይኸውም ራሳቸውን ከፍ ከፍ ያደረጉ ሁሉ ራሳቸውን እንዲያዋርዱ ይመከራቸዋል ለዚህም አሰረጅ ራሱ ክር ስቶስ ስለ እኛ ራሱን እንዳዋረደ ይገልጥላቸዋል፣ ይኽም መል እክት ስለ ክርስቶስ ፍጽም አምላክነትና ፍጽም ሰውነት የምት ናገር የሃይማኖት ትምህርት የተመላች መልእክት ናት።

ክርስቶስም ከአብ ጋር ትክክል እንደሆነ በመስቀልም መሞቱን ትንሣኤውን ዕርገቱን እንደገናም መጥቶ ይህን ዓለም ማሳለፉን ትናገራለች።

www.ethiopianorthodox.org

3ኛ. <u>የመልክቲቱ ዕውነተኛ ነት፤</u> ይህችን መልእክት ቅዱስ ጳውሎስ እንደጻፈት የውጭና የርኅጥ ምስክሮች አሉን፤

የውጭ አስረጅ የተባለው የሐዲስ ኪዳን አስ ተጋቢያች ሁሉ በአንድ ድምጽ ይሾች መልእክት የቅዱስ ጳውሎስ መልኦክት እንደሆነች ይመስክራሉ፤ ፖሊካርፖስ የተባለው ሐዋርያዊ አባት ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ በ3ኛው ምዕራፍ በጽሑፍ ይመስክሯል ። ኤር ኒያስ የተባለው አባትም እንዲሁ መስክሯል ። ከዚህ የበለጠ ግን የውስጥ ምስክር የተባለው ያስረዳል ይኸውም የዓረፍተ ነገሩ አሰካክ፤ የኃይለ ቃሉ አጣጣል የመልእክቶቹ መጀመሪያና መጨረሻ ሁሉ የቅዱስ ጳውሎስን ስም ባለሟያነቱ የርሱ መሆኑን ያስረዳል ።

<u>ምዕራፍ 9 ወደ ቆላስያስ ሰዎች የተላከች</u>

1. ከሌሎች ዕህች ቆላስቲያስ የተባለች አገር ያንዱ አስተዳዳሪ በሚሰራው አገር ውስጥ የምትገኝ ከተማ ናት ዕርስናም በቀደመው ጊዜ ትልቅ አንደነበረች በየጊዜው የተነሱ ሊቃውንት መስክረውሳታል፤ ሴሮ ደቱስ የተባለው ታሪክ ጸሐፊ ታሳቅ ከተማ ብሎ ሰይሟታል፤ በአርግጥም ብዙ ሕዝብ ገሪስች ይሁዱዎች የሐገረም ተወላጅዎች ስለ ሚኖሩባት ዘራቸው ተከልሰ ቋንቋቸው ወደ ዕብራይስጥ ተለውጠ ነበር ። ይሽችንም ቤት ክርስቲያን ቅዱስ ጳውሎስ ራሱ ሂደ አሳስ ተማራትም ምክንያቱም ይህች አገርና በርሷ የሚኖሩ ሰዎች በአርሱ ዘንድ እንግዳ መስለው ይታያሉና / ቆሳ. 2:2—8 /በኢጳፍራስም ሲገልጥ አንዲሁ ያስረዳል/ ቆሳ1:7/ቅዱስ ጳውሎስ በሁለተኛው ሐዋርያዊ ጉዞው አና በሦስተኛው የሐዋርያዊ ጉዞው/ የሐዋ.ሥራ 18—32 ::19:1/ በነዚህ በሁለቱ ጉዞዎች በአቅራቢያዋ አደለፈ ሲሔድ ከስ ተማራ ቸው ሕዝቦች የሰሙና ያመኑ ና ቸው ::

በተለይም ፊልሞናና ኤጳፋራስ አየተመሳለሱ ያስ ተማሯት ከተማ ና ት :: የሆኖ ሁኖ ሕዝቦ,ታ ከርሱ ሰዎ ተው አንደ አመኑ ስለ ሚቀጠሩ ቅዱስ ጳውሎስም ሲጽፍሳ ቸው ራሱ አንዳስ ተማራ ቸው አንደ እውነተኛ ፈጆ ቹ አድርጌ ነው ::

2ኛ. <u>መቼ፤ ወዴት፤ ለምን አንደ ተጻፈች፤</u> ይህች መልእክት የተጻፈች

አንደሌሎች መልእክቶች በመጀመሪያው አስራ ቱ ሮም ሳለ በግ ምት በ63 ዓመተ ምሕረት ነው :: የተጻፈችበት ምክንያት ቅዱስ ጳውሎስ በሮም ታሥሮ ሳለ የቆላስያስ ቤተ ክርስቲያን ጠባቂ

www.ethiopianorthodox.org

የሚሆን ኤጲፍራስ ወደ ሮም ሄደ በሕዝቡ ላይ የደረሰውን ብጥብጥ ለማቅመና ለማረጋጋት ነው :: ይኸውም ገኖስቲክስ የተባሉ መናፍቃን ተነስተው ቤተ ክርስቲያንን ያናውጡ ነበርና የክርስቲያን ልቡና ለጎዲይ ታውስ በማለት ነው/ ቀሳስ 2:8/ ::

ይህንን ጎርጥር በክርስቲያኖቹ ላይ አንዳመጣ ያደረጉ ይሁዴ ቻች ነበሩ /2:11-17/ እነዚህም መናፍቃን የሚያመልኩ እግዚአብሔርን ሳይሆን መሳአክትን ነበርና እነርሱ እግዚአብሔርን ለማምለክ ተፈጠረ እንጂ አማልክት አይደሉም ለማለት ጻፈ:: / ቀሳስ ያስ 1.16.2:15-19/ ደግሞም ገኖክቲክስ የተባሉ መናፍቃን እግዚአብሔር ረቂቅና መጡቅ ነው፤ ስለዚህ ይህን ዓለም ከፈጠረው ፍጹም ግንኙነት የለውም፤ [illegible] አያሉ ያስተምሩ ነበርና ሐሰቱን ለመግለጥ ቀሳስ 1.15-19/ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጽም ሰው ሁኖ የድኅነት ሥራን ፈጽሞ እንደሠራ በርሱም ፍጽሞ ድኅነት እንዳለ ለማስረዳት ነው :: ከዚህም ጋር ጋብቻ ርኩስ የሥጋ ተግባርን እንደ እንሰሳ እንፈጽማለን የሚሉ መናፍቃን ብለ ነበረ እነርሱን ለመዝለፍ የወንጌልን ትምህርት ለማረጋገጥ የጋብቻን ቅዱስን ዘርዘር የቤተሰብንም አሰተዳደር ጨምሮ ከሌሎች መልእክቶች ይልቅ በዚህ አስፋፍቶ ጻፈ/ ቀሳስ3.16-25/

3ኛ. <u>የመልክቲቱ ዐውነተኛነት፤</u> ወደ ቀሳስ ያስ የተሳከቸው መልእክት ርግጠኛ የቅዱስ ጳውሎስ እንደሆነች 2 ዓይነት ምክንያቶች አሉ ገኖው የውጭ ምስክር ነው ማለት በመሳ የቤተክርስቲያን አባቶች የተባሉ ለምሳሌ እነ ቀሌምናጠስ እነ ሰርዲሞስ እነ ቴዎፍሎስ በጽሑፍ አስረድተዋል ::

2ኛ የውስጥ ምስክር ራሱ መጻፉ በ3 ዓይነት የምስክራል ::

www.ethiopianorthodox.org

ሀ/ ራሱ ቅዱስ ጳውሎስ በአጼ ጳፍኩ ይላል/ ቆላስ 1.1/

ለ/ በውስጡ የሚገኘው ትምህርት የኮርስቶስ የባሕርይ አምላክነትን በሰፊው ሲያሶረዳ ዐረፍተ ነገረ የቅዱስ ጳውሎስ መሆኑን ይመሰክራል፤

ሐ/ በማንኛውም አኪኋን ይህች መልእክት ከፊልሞና መልእኮት ጋር ስለ ምትመሳሰል ጸሐፊው አንድ ሁኖ ባንድ ሰው እጅ መጻፉን ታረጋግጣለችና ይኸም ከሆነ የቅዱስ ጳውሎስ መሆኑ የታመነ ነውና ::

ምዕራፍ 10 ገኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች የተላከች

1. ተሰሎንቄ የምትባለው ሀገር የመቄዶንያ ነና ከተማ ናት ዛሬም የግራክ ሁለተኛ ከተማ እርሷ ናት :: የቀድሞ ስሟ ፋርሚ /ሞቃት/ የሚባል ነበር ምኮንያቱም በአቀራቢያዋ ፍልውሀ ስለነበር ነው :: ግን ንጉሥ ኪሣንድሮለስ የተባለው ከተማ ይቱን ከፍ ከፍ አደረጋት ስመጥረ ሁና በሮማውያን ሁሉ የታወቀች አደረጋት በሚስቱም ስም ተሰሎንቄ ብሎሰየማት :: ይኸች ከተማ ወደብ ነታ ለንግድ ተስማሚ በመሆኑ የዘመኑ ነጋዴዎች ከርሷ ወደ ኤፌሶንና ወደ ቆሮንቶስ ታላቅ ንግድ ነበራቸው በዚችውም ከተማ ይገኙ የነበረ ሕዝቦች ከግሪኮች ያቀር ሮማዊያንና ይሁዳዎች ነበረ :: በዚያ የሚገኙ ይሁዳዎች በቁጥር ከሁሉ ይበልጡ ስለነበር ቱልቁ ምኩራብ.ሰር ተው አየተሰበሰቡ ይጸልዩ ነበር፤ ብዙ አሕዛብንም ወደነሱ አምልኮት ይስቡ ነበር/ የሐ.ሥራ 16.1/ ቅዱስ ጳውሎስም በሁለተኛው የሐዋርያነት ጉዞው በ52 ዓ/ም ተሰሎንቄ በደረሰ ጊዜ በመጀመሪያ ወደ አይሁድ ምኩራብ ሄደ ስለ ክርስቶስ የሕይወት ታሪክ ነገራቸው ማለት ይመጣ ዘንድ ያለው መሲህ ክርስቶስ እንደሆነ ገለጠ አስተማራቸው :: / የሐ.ሥራ.17.3/ በዚያም በመዓልት ስለ ክርስቶስ እየተናገረ ፯ ሰምንት ያህል ቀየ፤ በሌሊት ግን የእጁ ሥራ እየሠራ የዐለት ፍሳጌቱን ያቅንና ከበር/1 ተሰሎ.2.9/

www.ethiopianorthodox.org

ቅዱስ ጳውሎስም በተሰሎንቄ ሲሰብክ እናትና አባቱ ለልጆቻ ተስማሚውን ነገር እንደሚሰጡ ተስማሚውን ነገር እንዲያውቁ እያለባበስ ያስተምራቸው ነበር፣ ደግ ባልንጀራም ባልንጀራውን እንዲመክር ትሕትናን በተመለ ከ ሲሰብካቸው እንደ ሰው ሳይሆን እንደ እግዚአብሔር መልእክት ክክብረው ተቀበሉት /1ተሰ.2.13/ :: ቅዱስ ጳውሎስ በመጀመሪያ ከተሰሎንቄ ሰዎች በሃይማኖት አድ ያደረጋቸው ክአሕዛብ ውስጥ ወደ አይሁድ ሃይማኖት የገቡትና ከገዢ ክፍል የተወለዱ ወንደቸና ሴቶች ናቸው /የሐ.ሥራ17.4/ ከወንደች ውስጥ አምነው ተጠምቀው የትረፋት አበጋዝ ለመሆን የበቁ አርስጠሮኮስ፣ ያሰን፣ሰኮንደስ ናቸው /የሐ.ሥራ.20.4/ :: የቅዱስ ጳውሎስ በክበት መልካም ፋሬን ለማፍራት በጀመረ ጊዜ ለምቀኝነት የማይመለሱ አይሁድ በጠላትነት ተነሳስተው በገበያውም ያሳደሙበት ጀመር/የሐ.ሥራ.17.5/ :: ቅዱስ ጳውሎስን በማንኛውም ነገር ሰያገኙት የርሱ ተከባካቢ የሆነውን ያሰን የተባለውን ሰው ይዘው ይደበድቡት ገበያ ለገበያም ይጎትቱት ጀመር፣ ቅዱስ ጳውሎስን እንዳይገድሉት ብለው ፈርተው በዚያች ሌሊት ክርስቲያኖች ከነተከታዮች አሸልከው ወደ ሴርያ ሳኩት፣ እንዲህ አደርጉ ያስተማራትን ቤተ ክርስቲያን በየጊዜው እየተመለለሰ ገብኝ ቷታል ::/የሐ.ሥራ 20.1.1 ጢሞ.1.3 /::

2ኛ/ <u>የዴትን መቼ፣ ለምን እንደተጻፈች፣</u> ይሽቸ መልእክት የተጻፈችበት አገር አቁና ነው፣ ቅዱስ ጳውሎስ ከተሰሎንቄ ወጥቶ አቴን በደረሰ ጊዜ ዋናውን አገልጋዩን ጢሞቲያስን በሳከው ጊዜ ይሽችን መልእክት ጨምሮ ልኮላቸዋል :: የተጻፈበትም ዘመን በግምት በ52 ዓ.ም ነው የተጻፈበትም ምክንያት ቅዱስ ጳውሎስ ከተሰሎንቄ በድንገት በብጥብጥ ምክንያት ወጥቶ ነበርና ኮዚያ የሚገኙ ክርስቲያኖች ችግር እንዳያገኛቸው ለማጽናናት ከደብዳቤውም ጋር በፍጽም ልቦናው የጫወደውን ጢሞቲያስን ሳከላቸው፣ ምክንያቱም ሰይጣን ይቃወማቸው እንደሆነ ይከጮ ከንቱ እንዳይሆን በቅርብ ለመረዳት ነው ::

www.ethiopianorthodox.org

በመጀመሪያ ጢሞቴዎስ መጥቶ አስደሰቸና አሳዘኝ ነገርን ነግሮት ነበርና ይሽን ለመጻፍ የሚአቦቃ ምክንያት ሰጠው/1 ተሰሎንቄ 3.6/ ጢሞቴዎስ ካመጣቸው አስደሳች ወሬዎች አንደኛው ምንም መከራውና ስደቱ ቢከዛባቸው የተሰሎንቄ ሰዎች ከሃይማኖታቸው አልተናወጡም አርስ በርሳቸው ካላቸው ፍቀር አልወጡም ቅዱስ ጳውሎስን አልረሱም ፣/ተሰሎንቄ 1.6/ አግሞ ቅዱስ ጳውሎስ የተሰሎንቄ ሰለ የክርስቶስን 2ኛ ጊዜ መምጣት አስተምሯቸው ስለነበር ፣ተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ክርክርን ፈጥሮ ነበርና ያንን ጸጥ ለማድረግ :: እንዲሁም የምጽአትን ነገር የመሰማታቸው ብዙዎች ከሥራቸው አየተፈናቀሉ ሥራ ፈት በመሆንና ለሌላም ሽኩም መሆናቸውን ነግሮት ነበርና ያልሠራ ሰው ሁሉ አይመገብ በማለት አነርሱን ለመገሠጽ/1 ተሰሎ.2.9/ :: ሰለዚህ ሰው ይግዛ የቀቢጸ ተስፋ ነገርን እያነሱ በጣም ያዘኑ ተስፋም ይቆርጡ ነበርና ይሽን የአሕዛብ ሥራ ኮርስቲያን ሊሰራው የማይገባ መሆኑን አየገለጠ ለመጻፍ /4.13--18/ በጠቅላላው የመልአክቲቱ ዋናው ዓላማ አማኒዎችን ፍጽማኑን ለማጽናናት ወጣ ገባ የሆኑትን ግን ለመገሰጽ ነው ::

3ኛ. <u>የመልአክቲቱ አውነተኛ ኑትፍ</u> ይሽኛ መልእክት ክአርገጥ ቅዱስ ጳውሎስ የጳፊት ለመሆኑ የውስጥና የውጭ አስረጅ ይገኛል፤ የውጭ ምስክር የሚሆን የቤተ ክርስቲያን አባቶች ወይም የሐዋርያት ተከታዮች የሆኑ ሁሉ በጽሑፍ አስረድተዋል ለምሳሌ አግናጥዮስ ምጥው ለአንበሳ ወደ ፖሊካርፖስ በጳፊው መልእክቱ ቀለምንጠስ ወደ ቆሮንቶስ በጳፊው መልእክቱ ሴረን ዮስ በለ መናፍቃን በጳፊው መልክቱ ... በሰፊው አስረድተዋል ::

ውስጣዊ አስረጅ 1ኛ ሪሱ ቅዱስ ጳውሎስ አንደጳፊው /1.1—18 ይነገረናል ::

2ኛውም አንደ ሌሎች መልእክቶች አረፍተ ነገሮችና የጽሑፍ አቅድና ስልት ያስረዳናል ::

www.ethiopianorthodox.org